# የሐዋርያት ሥራ

## ትምህርት አንድ

## የሐዋርያት ሥራ ዳራ

## The Book Of Acts

### Lesson One

### The BacKground of Acts

## ተርጓሚ፡እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ጸሐፊ**

የሉቃስ ወንጌል

ግልጽ/ውጫዊ

ስውር /ውስጣዊ

የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን

የእጅ ጽሁፎች

የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን መሪዎች

አዲስ ኪዳን

ስለ ጸሐፊው ጠቃሚ ፍንጮች

ሉቃስ

3. **ታሪካዊ መቼት / መቼ የት/**

ቀን

ከ70 ዓ.ም. በኋላ

ከ70ዓ.ም. በፊት

ቀደምት ተደራሲያን

ቴዎፍሎስ

ሰፊው ተደራሲያን

ማኅበራዊ አውድ

የሮሜ ግዛት

አይሁድ

4. **ነገረ-መለኮታዊ ዳራ**

ብሉይ ኪዳን

ታሪክ

እስራኤል

የእግዚአብሔር መንግሥት

የአይሁድ ነገረ-መለኮት

መጥምቁ ዮሐንስ

ክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮት

የሉቃስ ወንጌል

ኢየሱስ

ሐዋርያት

5. **ማጠቃለያ**

# 1. መግቢያ

ታላቁ ጀርመናዊ የሙዚቃ አቀናባሪ ሉድዊግ ቫን ቤትሆቨን በውብና ረቂቅ ቅንብሮቹ በመላው ዓለም ይታወሳል፡፡ ሙዚቃዊ ድሎቹ በራሳቸው አስደናቂ ቢሆኑም፣ በሥራዎቹ ይበልጥ የምትገረሙት ገና ከወጣትነት ዘመኑ ጀምሮ እየጨመረ በሚሄድ የመስማት ህመም ይሰቃይ የነበረ መሆኑን ስታስታውሱ ነው፡፡ እንዲያውም፣ ይበልጥ የሚያስገርመው ቤትሆቨን አብዛኞዎቹን ታላላቅ ሥራዎቹን የጻፈው ሙሉ በሙሉ በማይሰማበት ወቅት መሆኑ ነው፡፡ የቤትሆቨንን የሕይወት ዳራ ማወቅ በሙዚቃዎቹ የበለጠ እንድትገረሙ ያደርጋችኋል፡፡

ጠቃሚ በሆነ መንገድም፣ የቅዱሳት መጻሕፍት አድናቆታችን ቤትሆቨንን ከማድነቃችን ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የእግዚአብሔርን ራእይ የሚያውጁትን የመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ መጻሕፍት ኃይልና ግልፅነት በቀላሉ መመልከት አያዳግተንም፡፡ ሆኖም የመጽሐፍ ቅዱስን ጸሐፊዎች ዳራ፣ የኖሩበትን ዓለም፣ ሕይወታቸውንና ዓላማቸውን ስንመለከት ደግሞ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት አድናቆታችንና መረዳታችን የበለጠ ጥልቅ ይሆናል፡፡

ይህ ከሐዋርያት ሥራ ተከታታይ ትምህርታችን ይህ የመጀመሪያው ትምህርት ነው፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርት አምስተኛውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሐዋርያት ሥራ ብለን በተለምዶ የምንጠራውን መጽሐፍ እንመረምራለን፡፡ ይህንን ትምህርት "የሐዋርያት ሥራ ዳራ" የሚል ርእስ ሰጥተነዋል፡፡ የዚህን መጽሐፍ ትምህርቶች በጥልቀትና በግልፅነት በመመልከት ለመረዳትና ለማድነቅ የሚያግዙንን የተለያዩ መሠረታዊ ጉዳዮች እንመለከታለን፡፡

ትምህርታችን ሦስቱን የሐዋርያት ሥራ ወሳኝ ገፅታዎች ይዳስሳል፡፡  በመጀመሪያ፣ የመጽሐፉን ጸሐፊ ማንነት እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ታሪካዊ መቼቱን እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ነገረ-መለኮታዊ ዳራውን እንዳስሳለን፡፡ በጸሐፊው ማንነት እንጀምር፡፡

# 2. ጸሐፊ

እንደ ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም እስትንፈሰ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እስትንፋሰ መለኮትነቱ ግን ሰብዓዊ ጸሐፊዎቹን ቸል እንድንል ሊያደርገን አይገባም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቅዱሳት መጻሕፍት ከስህተት የነፁ እንዲሆኑ አድርጓል፣ ሆኖም የሰብዓዊ ጸሐፊዎቹን ስብዕና፣ ዳራ እና እሳቤ አብሮት እንዲኖርም አድርጓል፡፡

በትውፊት፣ የሐዋርያት ሥራ ፀሐፊነት ለሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ ለሉቃስ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ሦስተኛውም ወንጌል ሆነ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በግልጽ የጸሐፊውን ስም አልጠቀሱም፡፡ ስለዚህም፣ የሉቃስን ጸሐፊነት ትውፊታዊ ብይን ማፅናት የሚያስፈልግበትን ምክንያት መመልከት ይገባናል፡፡

የሐዋርያት ሥራን ጸሐፊነት ከሦስት አመለካከቶች አንፃር እንመረምረዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሐዋርያት ሥራን ከሉቃስ ወንጌል ጋር እናነጻፅራለን፡፡ ሁለተኛ፣ የሉቃስን ጸሐፊነት አስመልክቶ የመጀመሪያዩቱን ቤተክርስቲያን ታሪክና ምስክርነቷን እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ እነዚህን

መጻሕፍት ሉቃስ እንደጻፋቸው የሚያመለክቱ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ገፅታዎች በጥቂቱ እንመለከታለን፡፡ እስኪ በመጀመሪያ ከሉቃስ ወንጌል ስለ መጽሐፉ ጸሐፊ ምን እንደምንማር ወደ ማየቱ እንሸጋገር፡፡

# የሉቃስ ወንጌል

የሐዋርያት ሥራን ከሦስተኛው ወንጌል ጋር ስናነፃፅር፣ ሁለቱንም አንድ ጸሐፊ እንደጻፋቸው ሁለት ብርቱ መረጃዎችን እናገኛለን፡፡ በአንድ በኩል፣ በሁለቱም መጻሕፍት ከዚህ አቅጣጫ ግልፅ መረጃ የሚያቀርቡልን ሃሳቦች ተገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከመጻሕፍቱ ቅርፅ እና ይዘት ውስጣዊ መረጃም እናገኛለን፡፡ ሁለቱም መጻሕፍት የጋራ ጸሐፊ እንዳላቸው በሚያመለክተን ውጫዊ መረጃ እንጀምር፡፡

**ውጫዊ**

በሐዋርያት ሥራ ፩፥፩፣ በሐዋርያት ሥራ መቅድም ውስጥ፣ እንዲህ እናነባለን፡

> ***ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ኢየሱስ... ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ ጀመረው ሁሉ በመጀመሪያው በጽሐፍ ጻፍሁ፤ (የሐሥ ፩፥፩)***

በዚህ ስፍራ ጸሐፊው ስለ “መጀመሪያው መጽሐፉ” ይጠቅሳል፣ ይህም ማለት ቢያንስ ከሁለቱ መጻሕፍት የሐዋርያት ሥራ ሁለተኛው ነው ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የጻፈው ቴዎፍሎስ ለተሰኘ ሰው መሆኑንም ጠቅሷል፡፡ እስኪ በሉቃስ ፩፥1-4 የተጻፈውን ተመሳሳይ መቅድም አድምጡ፡

> **የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ ፩፥1-4)**

እንደገናም፣ ይህ ምንባብ ቴዎፍሎስ ስለተባለ ሰው ይናገራል፡፡ ከዚህ ስለሚቀድም መጽሐፍ ግን ምንም አልተጠቀሰም፡፡

የሐዋርያት ሥራና ሦስተኛው ወንጌል ለቴዎፍሎስ ተጽፈዋል፣ የሐዋርያት ሥራ ደግሞ “የቀደመውን መጽሐፍ” ያጣቅሳል፡፡ እነዚህ ጭብጦች የእነዚህ መጻሕፍት ጸሐፊ ቢያንስ ሁለት መጻሕፍትን እንደጻፈ፣ የሉቃስ ወንጌል የመጀመሪው እና የሐዋርያት ሥራ ደግሞ ሁለተኛው ስለ መሆናቸው ጠንካራ መረጃ ያቀርቡልናል፡፡ እንዲያውም፣ በእነዚህ ሁለት መቅድሞች የተገለፀው ተያያዥነት አንድ ጸሐፊ ሁለት ቅፆች ያሉት ሥራዎችን ሲሠራ የሚከተለውን ጥንታዊ የአፃፃፍ ልማድ

ይንፀባርቃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ኢዮሲበስ፣ *Against Apion* በተሰኘ ርዕስ ለጻፋቸው ሁለት መጻሕፍት ተመሳሳይ መቅድም ጽፏል፡፡

ከነዚህ ውጫዊ ትስስሮች በሻገር፣ በሐዋርያት ሥራና በሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ ተመሳሳይነት መኖሩን የሚያሳዩ ውስጣዊ ቁርኝቶችም አሉ፡፡ በርካታ የአዲስ ኪዳን መሁራን በሁለቱ መጻሕፍት መካከል መመሳሰሎች እንዳሉ አመልክተዋል፡፡ ጊዜ የሚፈቅድልን በጥቂቱ ብቻ እንድንመለከታቸው ቢሆንም፣ የጋራ ጸሐፊ እንዳላቸው ግን ወሳኝ ውስጣዊ መረጃ ያቀርቡልናል፡፡

## ውስጣዊ

እንደተመለከትነው፣ ሉቃስ 1፥1-4 ጸሐፊው በርካታ ምንጮችን የመረመረ መሆኑን እና ሁሉን በየተራ ለቴዎፍሎስ እንደጻፈለት ይገልፃል፡፡ ስለዚህ የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት በተመሳሳይ መንገድ ቅደም ተከተል እና ቅርፅ እንደያዙ በርካታ ምሁራን መጥቀሳቸው ሊያስደንቀን አይገባም፡፡ በተጨማሪም በመጻሕፍቱ አወቃቀርም ረገድ በርካታ መመሳሰሎች አሉ፡፡ መጻሕፍቱ በምዕራፍ በምዕራፍ የሚጓዙ ሲሆኑ፣ ተመሳሳይ መጠንም አላቸው፣ ሁለቱም ስታንዳርዱን የጠበቀ ጥቅል ሞልተዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ በሁለቱም መጻሕፍት መካከል ተመሳሳይ የዘመን ርዝማኔ አለ፡፡ ሉቃስም ሆነ የሐዋርያት ሥራ ተመሳሳይ ዓመታትን ይቆጥራሉ፡፡ መጻሕፍቱ ተጓዳኝ መሪ ሃሳቦችም አሏቸው፡፡ አንድ ምሳሌ ብናነሳ፣ መጽሐፉ ወደ ጡዘቱ የሚደርሰው ኢየሱስ ወደ መያዙ፣ ወደ ፍርድ መቅረቡ፣ ወደ መከራው፣ ወደሞቱና የይሁዲነት እና የአይሁድ ንጉሣዊ ኃይል መናገሻ በሆነችው በኢየሩሳሌም ድልን ለመቀዳጀት ባደረገው ጉዞ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም፣ የሐዋርያት ሥራ ወደ ፍፃሜው የሚመጣው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮም ባደረገው ጉዞ ሲሆን፣ መታሰሩን፣ ለፍርድ መቅረቡን እና መከራውን ከተረከ በኋላ የዓለም ንጉሣዊ ኃይል መናገሻ በሆነችው ከተማ የክርስቶስን ወንጌል በድል መስበኩን በመናገር ያበቃል፡፡

በተጨማሪ፣ በመጻሕፍቱ መካከል መመሳሰል አለ ምክንያቱም ሁለቱም የአንድ ታሪክ ክፍሎች ናቸውና፡፡ የሐዋርያት ሥራን እስከናገኝ ድረስ በሉቃስ ወንጌል ቀጥሎስ ምን ይሆን ይሆን ከሚል እውነታ ጋር እንደምንጋፈጥ ልናስብ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፣ በሉቃስ ወንጌል ጅማሬ ላይ፣ ኢየሱስ የአህዛብ ብርሃን እንደሆነ ታማኙ ስምዖን አውጇል፡፡ በሉቃስ 2፡30-32 የተፃፈውን አድምጡ፡

> **ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤**
> **ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።**
> **(ሉቃስ 2፡30-32)**

በሉቃስ ወንጌል የተገለጠው የኢየሱስ አገልግሎት ለእስራኤል ተሰጠውን የእግዚአብሔር የማዳን ተስፋ ያብራራል፡፡ ጉልህ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር ማዳን የአህዛብ ብርሃን ሆኖ ማገልገሉን የምናገኘው ግን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ነው፡፡ እነዚህና ሌሎችም መመሳሰሎች በሁለቱ ሥራዎች መካከል ያለውን የጋራ ቤዛዊ ታሪካዊ ራእይ እና የጋራ ዓላማና የእምነት አቋም ያላቸው

መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም መመሳሰሎቹ የአንድ ፀሐፊን ሥራዎች እንደምናይ ይነግሩናል፡፡

## የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን

የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት የጋራ ጸሐፊ እንዳላቸው የሚያመለክቱ ጥቂት መረጃዎችን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ያቆየችንን መረጃ እንመለከታለን፡፡ ከሁለተኛው እስከ አራተኛው የምህረት ምዕተ-ዓመት ድረስ የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን የሐዋርያው ጳውሎስ የጎዞ ባልደረባ የነበረው ሉቃስ፣ የሐዋርያት ሥራና የሉቃስ ወንጌል ጸሐፊ እንደሆነ መስክራለች፡፡ ይህንንም መረጃ በሁለት መንገድ እንፈታዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፉት ጥንታዊ ጽሑፎችን እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያን መሪዎች ስለ ሉቃስ ጸሐፊነት ምን እንደተናገሩ እንመለከታለን፡፡ አንዳንድ ጥንታዊ የእጅ ጽሁፍ ማስረጃዎችን በመመልከት እንጀምር፡፡

## የእጅ ጽሁፎች

ፓፒረስ የተሰኘ አንድ እጅግ ጥንታዊ የሆነ የእጅ ጽሁፍ፣ በ1952 (እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጣር) ዓ.ም. በግብጽ ውስጥ ተገኝቷል፡፡ የተጻፈው በፓፒረስ ላይ ሲሆን ጥንታዊ የሆኑትን ቀደምት የአዲስ ኪዳን የእጅ ጽሁፎችን በውስጡ አካቷል፡፡ ምናልባትም በእጅ የተገለበጠው በ175 እና በ200 ዓ.ም መካከል ሳይሆን አይቀርም፡፡ በውስጡም የሉቃስንና የዮሐንስን ወንጌላት አብዛኛ ክፍል ይዟል፡፡ በሁለቱ ወንጌላት መካከልም ይዘታቸውን የሚገልጥ መግለጫ ተቀምጧል፡፡ ከሉቃስ ወንጌል መደምደሚያ ቀጥሎ፣ የእጅ ጽሁፉ “*euangelion kata Loukan*” የሉቃስ ወንጌል የሚል ጽሁፍ ይዟል፡፡ ከነዚህም ቃላት ቀጥሎ “*euangelion kata Ioannan*” የዮሐንስ ወንጌል የሚል መግለጫ ተቀምጧል፡፡ “የሉቃስ ወንጌል” ከሚለው መግለጫ በፊት የነበሩት ጽሁፎች ሉቃስ የጻፈውን ወንጌል የሚያመለክት ነው፡፡ የእጅ ጽሁፉ የሚያመለክተው ገና ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑ እንደሚታመን ነው፡፡ የዚያ ቅጥያ ሆኖ ደግሞ፣ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራ ፀሐፊ መሆኑንም ያመለክታል፡፡

ሁለተኛ፣ ከ170 – 180 ዓ.ም. አካባቢ እንደተፃፈ የሚነገርለት፣ የሞራቶሪያኑ ቁራጭ፣ የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን አውቅና የሠጠቻቸውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ይዟል፡፡ የሉቃስ ወንጌል ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፣ የሐዋርያት ሥራም ጸሐፊ መሆኑን ለይቶ ገልጦታል፡፡ ከመስመር 34 እስከ 36 እንዲህ ይነበባል፡-

> **ከዚህም ባሻገር፣ የሐዋርያት ሥራ በአንድ መጽሐፍ ተጽፏል … ሉቃስ እርሱ በተገኘበት የተከናወኑ እያንዳንዳቸውን ድርጊቶች ሰብስቦ አስቀምጧቸዋል፡፡**

ይህ ዐረፍተ-ነገር የሚያመለክተው በሁለተኛው ምዕተ-ዓመት፣ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑ እና ቢያንስ በውስጡ ለተገለጡ ክንዋኔዎች ምስክር እንደሆነ በስፋት እንደሚታመን ይናገራል፡፡

ሦስተኛ፣ Anti-Marcionite Prologue ተብሎ የሚጠራውና ከ160 እስከ 180 ዓ.ም. ባለው ዘመን የተጻፈው የሦስተኛው ወንጌል መግቢያ የሉቃስን እና የሐዋርያት ሥራን ጸሐፊ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

**ሉቃስ፣ በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት፣ ይህንን ወንጌል አተናቅሮታል ... ከዚያም በኋላ ያው ሉቃስ የሐዋርያት ሥራንም ጻፈ፡፡**

ከነዚህ ጥንታዊ የእጅ ጽሁፎች ማስረጃ ባሻገር፣ የሦስተኛው ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን የመጀመሪያዩቱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አመልከተዋል፡፡

**የመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን መሪዎች**

ከ 130 እስከ 202 ዓ.ም. የኖረው የቤተክርስቲያን አባት ኢራኒየስ፣ የሦስተኛው ወንጌል ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን ያምናል፡፡ *Against Heresies በተሰኘው ሦስተኛው መጽሐፉ ምእራፍ 1 ክፍል 1 ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡-*

**የጳውሎስ ጓደኛ የሆነው፣ ሉቃስ፣ በጳውሎስ ተሰበከውን ወንጌል መዝግቦታል፡፡**

በዚህ ስፍራ ኢራኒየስ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጳውሎስ የሰበካቸውን የወንጌል መልእክቶች አስፍሯል ሲል አመልክቷል፡፡ እነዚህ ንግግሮቹ ወሳኝ ናቸው ምክንያቱም ጥሪ የሆኑት ታሪካዊ ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ስለ መጻፉ ኢራኒየስ የመጀመሪያ ደረጃ እውቀት አለውና ነው፡፡

ከ150 እስከ 215 ዓ.ም. የኖረው. የአሌክሳንደሪያው ክሌመንት፣ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን አመልክቷል፡፡ *Stromata ወይም ልዩ ልዩ ጉዳዮች* በተሰኘው በ5ኛ መጽሐፉ ምዕራፍ 12 ውስጥ፣ እንዲህ ጽፏል፡፡-

**ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጳውሎስ "የአቴና ሰዎች ሆይ፥ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ።" ሲል የተናገረውን አዛምዶልናል፡፡**

ከ155 እስከ 230 ዓ.ም. የኖረው ተርቱልያን፣ *Against Marcion* በተሰኘው አራተኛ መጽሐፉ ምዕራፍ 2 ላይ ይህንን ጽፏል፡

**ከሐዋርያቱ መካከል፣ ዮሐንስና ማቴዎስ እምነትን በውስጣችን አሳድረዋል.... ሉቃስና ማርቆስ ደግሞ ቆየት ብለው አድሰውታል፡፡**

በዚህ ስፍራ፣ ተርቱልያን ሦስተኛውን ወንጌል ለሉቃስ ሰጥቶታል፡፡

በመጨረሻም፣ ታላቁ የቤተክርስቲያን የታሪክ አዋቂ ኢዮሲበስ፣ *Ecclesiastical History* በተሰኘው ና በ323 ዓ.ም. በተፃፈው የመጀመሪያ መጽሐፉ ምዕራፍ 5 ክፍል 3 ውስጥ ሉቃስን የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ አድርጎ ጠቅሶታል፡፡ እስኪ ምን እንደጻፈ አድምጡ፡

**በሐዋርያት ሥራ የተመዘገበውን ቆጠራ ሉቃስ ጠቅሶልናል፡፡**

ከነዚህ የማረጋጋጫ ንግግሮች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያዩቱ ቤተ ክርስቲያን ሥነ-ጽሁፍ ውስጥ የሉቃስን ወንጌልና የሐዋርያት ሥራን ፣ ምንም እንኳን ለሐዋርያነት ባይለይም ከሉቃስ የተለየ ሌላ ሰው ጽፎታል የሚል አንድም እንኳን ማረጋገጫ አልተገኘም፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ፍንጮች

ምክንያት፣ የሉቃስን ጸሐፊነት የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ተመራምራ የደረሰችበት ሳይሆን፣ እውነት መሆኑ ታምኖበት የተቀበለችውን በቀጥታ ያስተላለፈች መሆኑን እንድናምን የሚያደርጉን የተለያዩ ምክንያቶች አሉን፡፡ ያም ሉቃስ ሁለቱንም መጽሐፎች የጻፈ መሆኑ ነው፡፡

## አዲስ ኪዳን

የሐዋርያት ሥራና ሦስተኛው ወንጌል የጋራ ጸሐፊ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ የሆነ ምክንያት እንዳለን ስንመለከት ቆተናል፣ የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን እንዳረጋገጠችውም ያ ብቸኛ ጸሐፊ ሉቃስ ነው፡፡ አሁን ደግሞ ከመረጃዎቹ በመነሳት ስለ ሉቃስ ስለ ራሱ ከተቀሩት የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ምን ድምዳሜ ላይ መድረስ እንደምንችል እንመለከታለን፡፡

ይህንን ማስረጃ በሁለት መንገዶች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ብቸኛው ጸሐፊ ከአዲስ ኪዳን የምናገኛቸውን ፍንጮች እንጠቅሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ እነዚህን ፍንጮች ስለ ሉቃስ ስለ ራሱ ካለን መረጃ ጋር እናነፃፅራቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ጸሐፊችን ያሉትን ፍንጮች እንመልከት፡፡

### ስለ ጸሐፊው ጠቃሚ ፍንጮች

ቀደም ብለን እንደተናገርነው፣ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ራሱን በስሙ አልጠቀሰም፡፡ እንደ እውነቱ፣ ለቅርብ ደጋፊው ለቴዎፍሎስ ስሙን መጥቀሱ አስፈላጊ አልመሰለውም፡፡ በሉቃስ 1፥3 ውስጥ፣ ልጽፍልህ "መልካም ሆኖ ታየኝ"፣ በሐዋርያት ሥራ 1፥1 ውስጥ ደግሞ፣ "በቀደመው መጽሐፌ .... ጻፍሁ" ብሏል፡፡ ጸሐፊው ይህ የቅርብ ደጋፊው እንደሚያውቀው ይናገራል፡፡ ይህ ነገር ለቴዎፍሎስ ምንም ችግር ባይፈጥርበትም፣ ለዘመናችን አንባቢወፐች ግን በርካታ ችግሮችን ይፈጥራል፡፡

በተመሳሳይም፣ አዲስ ኪዳንም ስለ ጸሐፊው የሚነግረን በርካታ ነገሮች አሉት፡፡ በመጀመሪያ፣ ሐዋርያ አልነበረም፡፡ እንዲያውም፣ ወደ እምነት የመጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ሳይሆን አይቀርም፡፡ እስኪ በሉቃስ ወንጌል 1፥1-2 የተጻፉትን ዝርዝሮች ተመልከቱ፡

> ***ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ (ሉቃስ 1፥1-2)***

ጸሐፊው የኢየሱስ ሕይወት ዝርዝሮች ወደ እኛ ተላለፉልን ብሎ ሲናገር፣ የኢየሱስ ሕይወት የዐይን ምስክር እንዳልነበረ እያመለከተ ነው፡፡

ሁለተኛ፣ የሐዋርያት ሥራ እና የሉቃስ ወንጌል የግሪክኛ አጣጣል ጸሐፊው ተማረ ሰው መሆኑን ያመለክታል፡፡ አብዛኞቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተለመደው መንገድ፣ እንዲያውም በጣም ባልተራቀቀው ግሪክኛ አጣጣል የተጻፉ ናቸው፡፡ ሆኖም የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ረቀቅ ያሉ ናቸው፡፡

ሦስተኛ፣ የሐዋርያት ሥራ ሁለተኛ አጋማሽ ጸሐፊው ከጳውሎስ የቅርብ የጉዞ ባልደረቦች አንዱ መሆኑን ያመለክተናል፡፡ በመጀመሪያዎቹ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች ውስጥ፣ ትረካው በዘላቂነት በሦስተኛ መደብ ተቀምጧል፡፡ ከሐዋርያት ሥራ 16 ጀምሮ ግን፣ ትረካው በአንደኛ መደብ ማለትም "እኛ" የሚል ቃል በመጠቀም ይቀጥላል፡፡ ይህንን መሳዩን ቋንቋ በሐሥ 16፥10-17፤ 20፥5-15፤21፥1-18 እና 27፥1-28፥16 ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህ ምንባቦች ጸሐፊው በጳውሎስ የመጀመሪያ ጉዞ እና ጳውሎስ ከቂሳርያ ወደ ሮም ሲጓዝ አብሮት የነበረ መሆኑን ያሳያሉ፡፡

እንግዲህ ስለ ጸገፊው ጥቂት ፍንጮችን ከተመለከትን፣ እነዚህ ዝርዝሮች ስለ ሉቃስ ከምናውቀው ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ እንመለከታለን፡፡

## ሉቃስ

ስለ ሉቃስ ወንጌልና ስለ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ የምናውቀውን አንድ ጊዜ እንመልከት፡፡ ሐዋርያ አልነበረም፡፡ በጣም የተማረ ይመስላል፡፡ የጳውሎስ የጉዞ ባልደረባ ነበር፡፡ እነዚህ ዝርዝሮች ስለ ሉቃስ ከምናውቀው ጋር እንዴት ይነፃፀራሉ? መልካም፣ ከሁሉ አስቀድሞ፣ ሉቃስ ሐዋርያ አልነበረም፡፡ ሐዋርያት በክርስቶስ እግር ተተክተው በቤተክርስቲያን ምሥረታ ሃላፊነት ያገለገሉ፣ ልዩ ሥልጣንም የነበራቸው እና ቤተክርስቲያንንም ከስህተትና ከችግር ይጠብቁ የነበሩ ናቸው፡፡ እንደ ሐሥ 1፥21-22 አባባል፣ ሐዋርያት ከኢየሱስ የተማሩ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ ሉቃስ ግን ኢየሱስን በአካል አግኝቶት አያውቅም ለሐዋርያት ተሰጥቶ የነበረውንም ዓይነት ሥልጣን አለኝ ብሎ አያውቅም፡፡ ይልቁኑ፣ የጳውሎስ ሚሲዮናዊ ጥረት ታማኝ ደጋፊ፣ የሐዋርያው አገልጋይ፣ ወይም ጳውሎስ በፊሊሞና 24 እንደገለፀው፣ "አብሮኝ ሠራተኛ" የሆነ ተብሎ ነው የተጠቀሰው፡፡

ሁለተኛ፣ ሉቃስ እጅግ የተማረ ይመስላል፡፡ ይህንንም በቆላስይስ 4፥14 ጳውሎስ ሉቃስን ሐኪም ብሎ በጠቀሰበት ውስጥ እናገኛለን፡፡ ህክምና በአዲስ ኪዳን ዘመን ዛሬ እንደሚሆነው ዓይነት መደበኛ ሥነ-ሥርዓት የነበረው ባይሆንም፣ ሆኖም አንድ ሰው ሐኪም ለመሆን ክህሎትና ተሰጥዖ ሊኖረው እንደሚገባ የታወቀ ነው፡፡

ሦስተኛ፣ ሉቃስ የጳውሎስ የጉዞ ባልደረባ የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ሉቃስ ከእርሱ ጋር ይጓዝ እንደነበረ በቆላስይስ 4፥14፤ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥11 እና በፊልሞና ቁጥር 24 ሐዋርያው ጳውሎስ ጠቅሷል፡፡

የሐዋርያት ሥራን ጸሐፊ ማንነት በዚህ መንገድ ማጠቃለል እንችላለን፡፡ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ሉቃስ መሆኑን የሚያመለክቱ ታላላቅ ታሪካዊ መረጃዎች አሉ፡፡ ሉቃስና የሐዋርያት ሥራ የጋራ ጸሐፊ አላቸው፡፡ የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ማስረጃዎች በጽናት የሚያመለክቱት የሉቃስን ጸሐፊነት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችም ከዚህ ሃሳብ ጋር ይጣጣማሉ፡፡ በእነዚህ መረጃዎች መሠረት፣ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራና የሉቃስ ወንጌል ጸሐፊ መሆኑን የምናምንበት በቂ ምክንያት አለን፡፡ ስለዚህ ሉቃስ ስለሚተርክለት ነገረ ጉዳይ ድንቅ እድልና ቅርበት እንደነበረው ዘወትር ልናስታውስ ይገባናል፡፡

# 3. ታሪካዊ መቼት/መቼ-የት

የሉቃስን ጸሐፊነት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ ታሪካዊ መቼቱ እንሸጋገራለን፡፡ ሉቃስ መቼ ጻፈ? መጽሐፉንስ ለማን አጠናቀረው?

የሐዋርያት ሥራን ታሪካዊ መቼት ስንመረምር፣ ሦስት ርዕሶችን እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሐዋርያት ሥራ የተቀናበረበትን ወቅት በመመልከት፣ ሉቃስ መቼ ጻፈው የሚለውን ጥያቄ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የመጽሐፉን ቀደምት ተደራሲያን እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የተደራሲያኑን ማኅበራዊ አውድ እንመረምራለን፡፡ እነዚህን ጉዳዮች መመልከታችን ለተተረኩት ጉዳዮች ሉቃስ የነበረውን ቅርበት በበለጠ መንገድ ለማብራራት ይረዳናል፡፡ በተጨማሪም ወንጌሉ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የነበረውን ተፅዕኖ በጠለቀና በተሟላ መንገድ እንድንረዳ ያስችለናል፡፡ መጽሐፉ የተጻፈበትን ቀን በመመልከት እንጀምር፡፡

## ቀን

የሐዋርያት ሥራ ለመጀመሪያ የተጻፈበትን ቀን አስመልክቶ የተለያዩ አመለካከቶች ቢኖሩም በጥቅል አነጋገር፣ የአዲስ ኪዳንን ምሁራን አስተያየቶች በሁለት መሠረታዊ አቅጣጫዎች እንከፍላቸዋለን፡፡ በአንድ በኩል፣ ሉቃስ የጻፈው በ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ከፈረሰ በኋላ ነው በማለት ጥቂቶች ይሟገታሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ ሌሎቹ ደግሞ የጻፈው በ70 ዓ.ም. ከመቅደሱ መፍረስ በፊት ነው ይላሉ፡፡ በአይሁድ ታሪክ ውስጥ፣ የ70ዓ.ም. አሰቃቂ ክስተቶች ወሳኞች ናቸው፣ በዚህም ምክንያት በእነዚህ ክስተቶች ላይ ስለ ተሰጡ ሃሳቦች መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ እነዚህን አመለካከቶች በየተራ እንመለከታቸዋለን፣ በመጀመሪያ ግን የጻፈው ከ70 ዓ.ም. በኋላ ነው የሚለውን እንመልከት፡፡

### ከ70 ዓ.ም. በኋላ

የሐዋርያት ሥራ ከ70 ዓ.ም. በኋላ ተጽፏል የሚሉ ምሁራን አመለካከታቸውን የሚመሠርቱት በርካታ ጉዳዮችን ከግምት በማስገባት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በርካቶች የሐዋርያት ሥራ ተስፋን ፈንጣቂ ገጽታ ከ80-90ዓ.ም እንደተጻፈ ያመለክታል ይላሉ፡፡ በዚህ አመለካከት፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለ መጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲን በጣም ቀናውን ብቻ ስለጻፈ ቀደም ብሎ ተጻፈ ለማለት ያዳግታል፡፡ ይልቁኑ፣ ከክስተቶቹ በርካታ ዘመናት ርቆ ስለመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ትዝታ ጽፏል ብንል ይሻላል፡፡ ግን ይህ አመለካከት የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የዘገበውን በውስጥና በውጭ የነበረ ችግር ያልተመለከተው ይመስላል፡፡

የሐዋርያት ሥራ ከ70 ዓ.ም. በኋላ ተጽፏል የሚሉ ሰዎች በአብዛኛው ይህን አቋም የሚይዙት፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ጽሑፎች የተመሠረቱት የአይሁድ ታሪክ ተመራማሪ በሆነው በኢዮሲበስ ሥራዎች ላይ ነው ብለው በማመናቸው ነው፡፡

የኢዮሲበስ አግባብነት ያላቸው ጽሁፎች ከ79ዓ.ም. በፊት አልተጠናቀሩም፣ ደግሞም ከ85 ዓ.ም. በፊትም በስፋት ሊሰራጩም አይችሉም፡፡ ስለዚህ፣ የሐዋርያት ሥራ በኢዮሲበስ ሥራዎች ላይ

የተመሠረተ ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች የሐዋርያት ሥራ ከ79 ዓ.ም. ምናልባትም ከ85 ዓ.ም. በፊት ሊጻፍ አይችልም በማለት ይደመድማሉ፡፡

የዚህ አቋም ጠበቆች በሐዋርያት ሥራና በኢዮሲበስ ሥራዎች መካከል በርካታ ግንኙነቶችን ቢያመለክቱም፣ ከጠቀሷቸው ግንኙነቶች መካከል አራቱን ብቻ እንዳስሳለን፡፡

በመጀመሪያ፣ የሐሥ 5፥36 ቴዎዳስን ይጠቅሳል፣ ይህ የአይሁድ አብዮተኛ *Antiquities* በተሰኘው 2ኛ መጽሐፉ ክፍል 97 ውስጥ ሳይጠቅሰው አይቀርም፡፡ ሁለተኛ፣ የሐሥ 5፥37 አብዮተኛውን የገሊላውን ይሁዳን ይጠቅሳል፣ እርሱም *Jewish Wars* በተሰኘው 2ኛ መጽሐፉ ክፍል 117 እና 118 እና *Antiquities*. በተሰኘው 18ኛ መጽሐፉ ከክፍል 1-8 ውስጥም ይገኛል፡፡ ሦስተኛ፣ በሐሥ 21፥38 ግብፃዊ የተሰኘው ሽፍታ *Jewish Wars በተሰኘው 2ኛ መጽሐፉ ክፍል 261 እስከ 263 ውስጥ እና Antiquities* በተሰኘው 20ኛ መጽሐፉ ክፍል 171 ውስጥ ይገኛል፡፡ አራተኛ፣ በሐዋርያት ሥራ 12፥19-23 የተጠቀሰው የሄሮድስ ሞት መግለጫ የተመሠረተው *Antiquities* በተሰኘው በኢዮሲበስ 19ኛ መጽሐፉ ክፍል 343 እስከ 352 ላይ ነው በማለት ብዙ ቁጥር ያላቸው ተርጓሚዎች ይከራከራሉ፡፡

ይህንን የአመክንዮ መስመር የሚከተሉ ተርጓሚዎች በርካታ ቢሆኑም፣ በሐዋርያት ሥራና በኢዮሲበስ ጽሁፎች መካከል ተዛማጅ ነገሮች አሉ ማለት የሐዋርያት ሥራ በኢዮሲበስ ሥራዎች ላይ ለመደገፉ ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲያውም፣ በሐዋርያት ስራ ስለ ሁኔታዎቹ የተሰጠው መግለጫ ከኢዮሲበስ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ነገሩ የሚመስለው በየግላቸው ታዋቂ የሆነ ታሪካዊ ክንዋኔን ደግመው ገልጠውታል ወይም በጋራ ምንጭ ተጠቅመዋል የሚለው ነው፡፡ የተጠቀሱት ሰዎች ታዋቂና ታሪክ የሚያወሳላቸው እስከሆኑ ድረስ፣ ከአንድ ታሪካዊ ዘገባ በበለጠ ሊጠቀሱ መቻላቸው አያስደንቅም፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን፣ ከቴዎዳስ አንፃር፣ በጣም የጠለመደ ስም እየጠቀሰን ነው፡፡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች አንድ ዓይነት ስም ሊጠቀሙም ይችላሉ፡፡

## ከ70 ዓ.ም. በፊት

የሐዋርያት ሥራ ስለተጻፈበት ወቅት ሁለተኛው አመለካከት በ70 ዓ.ም. ከመቅደሱ መፍረስ በፊት ተጽፏል የሚለው ነው፡፡ ይህንን ቀደምት ቀን የሚደግፉልን በርካታ መረጃዎች አሉን፣ ለአሁኑ ግን በሐዋርያት ሥራ የመጨረሻ ትዕይንት ልናጠቃልል በምንችለው ላይ እናተኩራለን፡፡

በሐዋርያት ሥራ 28፥30-31 የተጠቀሱትን ሁለት ቁጥሮች እስኪ አድምጡ፡፡ በዚያ ስፍራ ሉቃስ ስለ ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፡፡

> **ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፤**
> **ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር።** (ሐሥ 28፥30-31)

የሐዋርያት ሥራ የሚደመደመው ጳውሎስ በተከራየው ቤት በእስር ላይ ሆኖ ክርስቲያናዊውን ወንጌል በድፍረት መስበኩን በመተረክ ነው፡፡ ይህ መደምደሚያ የሐዋርያት ሥራ ከ70 ዓ.ም. በፊት ስለመጻፉ ጠቃሚ መረጃ ይሰጠናል፡፡

በመጀመሪያ፣ ሉቃስ ስለ ጳውሎስ አገልግሎት የሰጠው መግለጫ በ64 ዓ.ም. የተከናወነውን ወሳኝ ክስተት ሳይዘግብ ያበቃል፡፡ በ64ዓ.ም.፣ በሮም ከተማ ውስጥ ስለተነሳው አስደንጋጭ እሳት ኔሮ ክርስቲያኖችን ተጠያቂ በማድረግ ያሳድዳቸው ጀመር፡፡ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ከመጻፉ በፊት ይህ ተከስቶ ከነበረ አለመጥቀሱ እንግዳ ነገር ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ተሰውቷል ተብሎ የሚታሰበው ኔሮ ቤተክርስቲያንን ሲያሳድድ በነበረበት፣ ምናልባትም በ65 ዓ.ም. ወይም ከዚያ ብዙ ሳይርቅ እንደሆነ ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራ ከዚህ በኋላ የተጻፈ ከሆነ፣ የመጽሐፉ ዐቢይ ገፀ-ባህርያት ከሆኑት አንዱ የሆነውን ሰው መሰዋት በእርግጠኝነት ይዘግበው ነበር፡፡

ሦስተኛ፣ በ70 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም የሚገኘው የአይሁድ መቅደስ ሲደመሰስ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን የአይሁድና የአህዛብ ክርስቲያኖች ግንኙነት በእጅጉ አውኮታል፡፡ የሐዋርያት ሥራ ስለነዚህ ግንኙነቶች በብዙ ስፍራዎች አውስቷል፡፡ ስለዚህም፣ ይህንን የመቅደሱን መፍረስ ሳይዘግብ ቸል ብሎ የማለፉ ነገር ጨርሶ እንግዳ ነው የሚሆነው፡፡

በእነዚህ እውነታዎች ብርሃን ሰጪነት፣ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የደመደመው በመጽሐፉ ላይ በተጠቀሰው ታሪካዊ ዝርዝር መሠረት ጳውሎስ በሮም በእስር ላይ ሆኖ አገልግሎት ይሰጥ በነበረበት ወቅት ማለትም ከ60 እስከ 62 ዓ.ም. ነው ብሎ መደምደም ከሁሉ የተሻለ ነው፡፡

# ቀደምት ተደራሲያን

የሐዋርያት ሥራ ተጻፈበትን ይህንን ቀደሚ ጊዜ በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ሁለተኛው የሐዋርያት ሥራ ታሪካዊ መቼት ገፅታ እንሸጋገር፡ ያም የሉቃስ ቀደምት ተደራሲያን ናቸው፡፡ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሊደርሳቸው ያሰባቸውን ተደራሲያን ማወቅ መጽሐፉን ለመረዳት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

የሐዋርያት ሥራን ቀደምት ተደራሲያን በሁለት መንገዶች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መጽሐፉ ለተይቶ ለቴዎፍሎስ መጻፉን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ መጽሐፉ ከዚያም ሰፋ ያሉ ተደራሲያንን ሊያካትት የሚችል መሆኑንም እናያለን፡፡ አስቀድምን የሉቃስ ቀዳሚ አንባቢ ከሆነው ከቴዎፍሎስ እንጀምር፡፡

## ቴዎፍሎስ

የሉቃስ መቅድም እንደሚያሳየን ቴዎፍሎስ፣ ጽሑፎቹን ለእርሱ ለይቶ አድራሻ ያደረገለት የእርሱ የቅርብ ሰው ነው፡፡ በሉቃስ ፩፥3 እና በሐሥ ፩፥፩ እንደምንመለከተው፣ ሉቃስ ጽሁፎቹን አድራሻ ያደረገው ለቴዎፍሎስ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር፣ በሉቃስ ፩፥3 ውስጥ፣ ሉቃስ ቴዎፍሎስን እጅግ የከበርህ ይለዋል፡፡ ሉቃስ የተጠቀመው ቃል “እጅግ የከበርህ” የሚለውን ሲሆን (በግሪክኛው kratistos) ከበሬታን ያመለክታል፡፡ ይህ ቃል ቴዎፍሎስ እጅግ ባለጠጋ የነበረ የቅርብ ደጋፊው ነው ብለው በርካቶች እንዲያምኑ አድርጓቸዋል፡፡

በሉቃስና በቴዎፍሎስ መካከል የነበረው ግንኙነት ግን ከዚህ እጅግ የሰፋና ከቅርብ አጋርነት የዘለለ ነበር፡፡ የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያ ሥራን መጻሕፍት በማንበብ፣ ቴዎፍሎስ የሉቃስ ተማሪ ሆኗል፡፡ የዚህን ቴዎፍሎስ ከሉቃስ ጋር የነበረውን ግንኙነት ገፅታ በሉቃስ ወንጌል መግቢያ ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡

በሉቃስ 1፥3-4 ውስጥ እንዲህ እናነባለን፡

> **እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ 1፥3-4)**

ይህ ምንባብ እንደሚያሳየው፣ የሉቃስ ወንጌል በአንድ ጎኑ የተጻፈው ቴዎፍሎስ ስለተማራቸው ነገሮች እርግጡን እንዲያውቅ ለማስቻል ነበር፡፡ በአጭሩ ብናስቀምጠው፣ ሉቃስ የጻፈው ቴዎፍሎስን ለማስተማር ነው፡፡

ሉቃስ ነፀሎ ቴዎፍሎስን እንደ መጀመሪያ አንባቢው ማቅረቡን ከተመለከትን፣ የሉቃስን ተደራሲያን ከዚያ በሰፋ ሁኔታ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

## ሰፊው ተደራሲያን

በአዲስ ኪዳን በሆነ ስፍራ ስናነብብ፣ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የነበረችው  ሰፊይቱ ቀደምት ቤተክርስቲያን ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ በጠቀሳቸው በርካታ ጉዳዮች ውስጥ በትግል ውስጥ እንደነበረች መመልከት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ የሉቃስ ትረካ በተለያዩ ሐዋርያትና መምህራን አመራር ምክንያት በአይሁድና በአህዛብ አማኞች መካከል የነበረውን ሽኩቻ እና መከፋፈል ይጠቅሳል፡፡ ዘገባው በሐሰት መምህራን እየተገለጡ የመጡትን የአስተምህሮ ህፀፆችንም ይነካካል፡፡ በተጨማሪም የሐዋርያት ሥራ በቤተክርስቲያንና በመንግሥት መካከል የነበረውን ግጭትም ይነካል፡፡ ሴቶችና ድሆች በገጠሟቸው ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡  ስደት፣ መከራና መታሰርንም ይዘግባል፡፡ የሐዋርያት ሥራ እነዚህን የአስተምህሮ፣ የግብረገብ እና ተግባራዊ እንቅፋቶች ይዘግባል፣ ምክንያቱም የመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ ዐሥርት ዓመታት ተመሳሳይ ትግሎች ነበሯትና ነው፡፡

ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የጻፈው በጣም ሰፊ ጉዳዮችን ለመዳሰስ እስከሆነ ድረስ፣ መጽሐፉ በበርካታ አንባቢዎች እንዲነበብ መሻት እንደነበረው ማሰቡ አግባብነት አለው፡፡ ቴዎፍሎስና በስፋት ደግሞ የመጀመሪያዩቱ ቤተክርስቲያን በርካታ ተግዳሮቶችን እንዴት እንደሚጋፈጡ የማገዝ ሸክም ነበረው፡፡

# ማኅበራዊ አውድ

የሐዋርያት ሥራን ቀንና ቀደምት ተደራሲያን ከተመለከትን፣ ሦስተኛውን ጉዳይ ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጻፈበትን ዓለም ገፅታ፣ ማለትም የሉቃስን ወንጌል አጠቃላይ ማኅበራዊ ገፅታ እንመለከታለን፡፡ በሉቃስ ዘመን ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ማኅበረሰባዊ ኃይላት በተረዳን መጠን፣ የመጽሐፉን በርካታ ገፅታዎች ለመረዳት ይበልጥ እንታጠቃለን፡፡

የሐዋርያት ሥራን ማኅበራዊ አውድ የመጀመሪያዪቱን ቤተክርስቲያን ሕይወት ማዕከላዊ ሁለት ገፅታዎች በመመልከት እንመረምረዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሮሜን አገዛዝና ኃይል፤ ሁለተኛ ደግሞ፣ በቤተክርስቲያንና በአይሁድ መካከል ስነበረው አዲስ ግንኙነት እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ የሮምን ግዛት እንመልከት፡፡

## የሮም ግዛት

ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን በጻፈበት ወቅት፣ የሮም መንግሥት ሜድታራኒያኑን ዓለም በጠቅላላ ድል ያደረገበትና የተቆጣጠረበት፣ እስከ አሁኗ ብሪታኒያ፣ሰሜን አፍሪካና እስከ እስያ ጥቂት ክፍሎች ድረስ የተስፋፋበት ጊዜ ነበር፡፡ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ዘመንም፣ ግዛቱ አሁንም እየሰፋ ሄደ፣ በርካታ ግዛቶችንም በስሩ አስገባ፡፡ ስለዚህም፣ የሮሜ መንግሥት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በሮማዊ እሴቶች፣ ግቦች እና የእምነት አቋሞች በጥልቀት ተፅእኖ አሳደረ፡፡

ያለምንም ጥርጥር፣ ሮም ድል ባደረጋቸው ግዛቶቹ ውስጥ የሚያሳድረገው ትልቅ ተፅዕኖ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ነው፡፡ ከሮም መንግሥት ዋነኛ ፖለቲካዊ ጥረቶች አንዱ በግዛቱ ውስጥ ያሉ አገራትን ባለሥልጣናት በኃይል በመጫን ሰላምንና ተአማኒነትን ማስፈን ነበር፡፡

ድል የተደረጉ መንግሥታትም መጠነኛ የአገር ውስጥ ሥልጣን አላቸው፣ የአገር ውስጥ መንግሥታቸው ግን ዘወትር ለሮም የሥልጣን ተዋረድ ተገዢ የመሆናቸው ነገር ይቃኛል፡፡ ለምሳሌ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ፊሊክስ እና ፊስጦስ የተባሉ ሁለት የቂሳርያ የሮም ባለሥልጣናትን ገልጧል፡፡ እነርሱም በቂሳርያ ተቀምጠው አጠቃላዩን የይሁዳ ግዛት ይገዛሉ፡፡ የግብሩን ሥረዓት ከመቆጣጠር ባሻገር፣ በግዛቶቻቸው ስር ባሉት መንግሥታት ሰላምና ሥርዓት እንዲሰፍን የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

አገዛዙ በተጨማሪም የሮሜ ዜጎችን ድል ካደረጋቸው አገሮች ዜጎች ጋር በማቀላቀል ባህላዊና ፖለቲካዊ ተፅእኖም ፈጥሯል፡፡

ሮም በተደጋጋሚ፣ አዲስ ድል ባደረገችባቸው ግዛቶች ውስጥ ጡረታ ለሚወጡ ወታደሮቿ መሬት ትሰጣለች፡፡ ይህ ልምድ በግዛቶቿ ሁሉ ውስጥ ታማኝ የሆኑ ዜጎች በማኅበረሰቡ መካከል እንዲኖሯት ያስቻለና በመንግሥታዊም ሆነ በማኅበራዊ መዋቅሮች ውስጥ የሮሜን እሴቶች እንዲያስተዋውቁ አድርጓል፡፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በየጊዜው የሮምን ሰዎች የሚጠቅሰው ለዚህ ነው፡፡ ገና በጰንጠቆስጤ ማግሥት፣ በሐሥ 2፥10-11 ውስጥ "በሮሜም የምንቀመጥ፥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን፥… " ተብሎ እናነባለን፡፡ እንደገናም፣ በሐሥ 10 ውስጥ፣ በሐዋርያት ሥራ ለተጠቀሰው የወንጌል መስፋፋት ትልቅ ሚና ስለ ነበረውና ፈሪሃ እግዚአብሔር ስለነበረው ስለ ቆርኔሌዎስ እናነባለን፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ የሀገሬው ባህል በሮሜ ሥራዎች ማለትም፣ መንገዶች፣ ትላልቅ ህንፃዎችና የህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ተፅዕኖ ስር ይወድቃል፡፡ ይህ የሮም አገዛዝ ገፅታ ጳውሎስና ሌሎች በሚያደርጉት ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ በነፃነትና ያለስጋት እንዲንቀሳቀሱ አስችሏቸዋል፡፡ ሐዋርያትም ከስፍራ ወደ ስፍራ ሲንቀሳቀሱ ወንጌልን ለመስበክ እነዚህን የህዝብ መሰብሰቢዎች ይጠቀማሉ፡፡

ለቀደመችው ቤተክርስቲያን የሮም አገዛዝ ያስገኘላት ሌላው ወሳኝ ገፅታ ድል ባደረገቻቸው ህዝቦች ሃይማኖት ላይ ያሳደረችው ተፅዕኖ ነው፡፡

ሉቃስ በጻፈበት ዘመን፣ በሮሜ አገዛዝ ማዕከል ላይ አንድ ሰው ነበር፡፡ እርሱም ቄሳር ነው፡፡ ንጉሥ ቄሳር የህዝቡና የግዛቱ ጌታ ብቻ ሳይሆን፣ የህዝቡ አዳኝም ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡ የሮሜ ፕሮፓጋንዳ እንደሚጠቅሰው፣ ቄሳር ህዝቡን ከቀውስና ከጨለማ አድኗል፡፡ ስለዚህም የሮም መስፋፋት የማዳኑ መስፋፋት፣ ህዝቡን ከአገራቸው ነገሥታት ጭቆና ነጻ በማውጣት እያንዳንዱን ሰው ወደ ሮም የበጎ አድራጎት መንግሥት ማሸጋገር እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

በአብዛኛዎቹ ስፍራዎች፣ ድል የተደረጉት ህዝቦች በርካታ ሃይማኖታዊ ስርዓቶቻቸውን እንዲፈፅሙ ይፈቀድላቸዋል፣ ሆኖም የቄሳርን እና ትውፊታዊ የሮሜ ጣዖታትን የበላይነት ሊያውጁ ግን ይገባል፡፡ እንግዲህ፣ በብዙ መንገዶች፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ በርካታ አይሁድና ክርስቲያኖች በከበሬታ ለሮም ተገዢ ሲሆኑ፣ ታማኝ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ግን የሮሜን ሃይማኖት የበላይነት እውቅና አልሰጥ አሉ፡፡ የሮም መንግሥት የአይሁድን እምነት እንደ ህጋዊ ሃይማኖት ቢቀበለውም ደግሞም የክርስትናን እምነት በተቻለ መጠን ለቀቅ ቢያደርገውም፣ ሁለቱንም ቡድኖች መጨቆኑ ግን አልቀረም፡፡

የመንግሥት አስተዳደሩን፣ ህዝቡን፣ የህዝብ እንቅስቃሴዎችንና ሃይማኖቱን በመቆጣጠር፣ ተፅዕኖውን በተቻለው ስፍራ ሁሉ ለማስፋፋት ሞከረ፡፡

የሐዋርያት ሥራን ማኅበራዊ አውድ ከሮሜ መንግሥት ተፅዕኖ አንፃር ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ሉቃስ በጻፈበት ወቅት ስለነበረው ሌላኛው ወሳኝ ማኅበራዊ ገጽታ ማለትም በማያምኑ አይሁድና በመጀመሪያዪቱ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት እንመረምራለን፡፡

## አይሁድ

በአይሁድና በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን መካከል የነበረውን ግንኑነት አስቀድመን በመካከላቸው የነበረውን ጥልቅ ትስስር በመመልከት እንዳስሳለን፣ ሁለተኛ ደግሞ መሠረታዊ ልዩነቶቻቸውን እንቃኛለን፡፡ በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረውን ትስስር በመመልከት እንጀምር፡፡

የቀደመችው ቤተክርስቲያን ከአይሁድ ጋር የምትጋራው የጋራ ቅርስ ነበራት፡፡ በዚህ ዘመን የምንኖር ሰዎች ራሳችንን መልሰን መላልሰን ልናስታውሰው የሚገባን ነገር ኢየሱስ አይሁድ የነበረ መሆኑን፣ ሐዋርያትም በጠቅላላ አይሁድ እነደነበሩ፣ በጅማሬ ላይም፣ ቤተክርስቲያን ራሷም አብዛኛው አይሁድ አማኝ የነበረባት መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ፣ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ልቡና ውስጥ፣ ተስፋ የተገባለት የአይሁድ መሲህ ለይሁዲነት የተገለጠ ታማኝነት እንዲያሳይ መጠበቃቸው ሊያስገርመን አይገባም፡፡

እንደ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አገላለጥ፣ በቀደመችው ቤተክርስቲያን የነበሩ አብዛኞቹ አማኞች በመቅደስ አምልኮ ውስጥ ይሳተፉ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመማር በምኩራብ ይገናኙ እና ለበርካታ የአይሁድ ልማዶች አድናቆታቸውን መግለጣቸውን ይገልጡ ነበር፡፡

ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 13፥32 የተናገረውን አድምጡ፡

*እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምስራቹን ለእናንተ እንሰብካለን፤ (የሐሥ 13፥32)*

ጳውሎስና ከእርሱ ጋር ይጓዙ የነበሩት ሁሉ በምኩራብ ከሚገኙ አይሁድ ጋር ራሳቸውን በማስማማት፣ የቀደሙትን አባቶች "**አባቶቻችን**" እኛን ደግሞ እንደ ልጆች ይጠሩናል፡፡

በተጨማሪም፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያንና የአይሁድ ማህበረሰብ በሰፊው ተመሳሳይ ለሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ በአይሁድ ማኅበረሰብ አውድ ወንጌልን ሲሰብኩ ክርስቲያኖችን ዘወትር ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይስቧቸው ነበር፡፡

በሐዋርያት ሥራ 17፡1-3 ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ለአይሁድ ሲያውጅ ቅዱሳት መጻሕፍትን መጥቀሱ ተመዝግቧል፡፡ ሉቃስ በዚያ ስፍራ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***በአንፊጶልና በአጶሎንያም ካለፉ በኋላ ወደ ተሰሎንቄ መጡ፥ በዚያም የአይሁድ ምኵራብ ነበረ።***
> ***ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፥ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር፤***
> ***ሲተረጕምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ። ይህ እኔ የምሰብከላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር።***

ከዚህም ባሻገር፣ በይሁዲነት እና በክርስትና መካከል ያለው ጥልቅ ግንኙነት በአይሁድ ባለሥልጣናትና በቀደመችው ቤተክርስቲያን መካከል ጉልኅ ንክኪ እንዲኖር አድርጓል፡፡

እንደ ሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አገላለጥ፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያን የክርስቶስን ወንጌል ከመስበክ አንፃር የነበራት ቁርጠኝነት በተደጋጋሚ ጊዜ ከአይሁድ አለቆች ጋር ወደመጋጨት አድርሷታል፡፡ በተቻለ መጠን ግን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንዲተላለፉ ካላዘዟቸው በስተቀር የቀደሙት ክርስቲያኖች የአይሁድን መሪዎች እውቅና ይሰጧቸው ነበር፡፡

በአይሁድና በቀደመችው ቤተክርስቲያን መካከል የነበረው ጥልቅ ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሳለ፣ መሠረታዊ ልዩነቶችም ነበሯቸው፡፡

የመጀመሪያውና ከሁሉም መሠረታዊ የሆነው፣ ክርስቲያኖችና የማያምኑት አይሁድ በኢየሱስ ማንነትና ሥራ አይስማሙም ነበር፡፡ ኢየሱስ ሞትን ድል ያደረገና ፍጥረትን ሁሉ የሚያድስ፣ ይህንንም በገዛ ትንሣኤው ያስመሰከረ መሲህ መሆኑን ቤተክርስቲያን ትሰብካለች፡፡ ለማያምኑት አይሁድ ግን እንደ ወንጀለኛ የተሰቀለን ሰው መሲህ ነው ማለት ፈፅሞ የማይታሰብ ነው፡፡ ይህም ልዩነት በአይሁድና በክርስቲያኖች መካከል እስከዚህ ዘመን ድረስ የዘለቀ ክፍተትን ፈጥሯል፡፡

ሁለተኛ፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያንና የአይሁድ መሪዎች በዕብራውያኑ መጽሐፍ ሥልጣን ላይ ቢስማሙም፣ በተለይ ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ በተጠቀሱ የዕብራውያን መጻሕፍት ትክክለኛ አተረጓጎም ረገድ ግን የከረረ ጠብ ነበራቸው፡፡ በዕብራውያኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መፃኢው

መሲህ የተነገሩት ተስፋዎች በኢየሱስ አማካይነት እንደተፈፀሙ የቀደመችው ቤተክርስቲያን ስታምን፣ የማያምኑት አይሁድ ግን ይህንን መረዳት ይክዳሉ፡፡ በይሁዲነት በራሱ ውስጥ በርካታ አመለካከቶች ቢኖሩም፣ አብዛኞቹ ግን የብሉይ ኪዳንን ተስፋዎች ኢየሱስ ፈፅሟቸዋል የሚለውን መቀበል አልቻሉም፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ፣ የመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የአይሁድ ህዝብና የቀደመችው ቤተክርስቲያን ስለ አህዛብ ባላቸው አመለካከትም ይለያዩ ነበር፡፡ አብዛኛውን ጊዜ፣ አክራሪ አይሁዶች ከአህዛብ ጋር አይተባበሩም ነበር፡፡ በሌላ ወገን ግን፣ በርካታ ያልተገረዙ አህዛብ በይሁዲነት አስተምህሮዎችና እምነቶች ከመሳባቸው የተነሳ በየአጥቢያው ከሚገኙ የአይሁድ ምኩራቦች ጋር ራሳቸውን አቆራኝተው ስለ ነበር እግዚአብሔርን የሚፈሩ ተብለው ይታወቁ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩቱ ከሌሎቹ አህዛቦች በላይ የሚከበሩ ሲሆኑ፣ የአይሁድ ማኅበረሰብ ሙሉ አባል ግን አልነበሩም፡፡ አህዛብ አማኞች ወደ ይሁዲነት ገብተው ነበር፣ ግን እንደ ጥምቀት፣ መገረዝና የአይሁድን ትውፊቶች የመጠበቅን ግዴታም ይዞባቸው ይመጣ ነበር፡፡

የቀደሙትም አይሁድ ክርስቲያኖች ስለ አህዛብ ይህንኑ ተመሳሳይ መረዳት ይዘው ቢነሱም፣ ቀስ በቀስ ግን ክርስቶስን የተከተሉ አህዛብ በክርስቲያን ቤተክርስቲያን ውስጥ ባለሙሉ መብት መሆናቸውን እየተረዱ መጡ፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ በተቀበሉት አዲስ መገለጥ መሠረት፣ በአንደበት በሚነገር ምስክርነት የተረጋገጠ እምነትና መጠመቅ ለክርስቲያን ቤተክርስቲያን አባልነት ብቁ መሆኑን የቀደመችው ቤተክርስቲያን ወሰነች፡፡ ስለዚህም ሐዋርያት ክርስቶስ እርሱ የአይሁድም የአህዛብም ጌታ የመሆኑን ወንጌል ማወጅን ልምምዳቸው አደረጉት፣ ቤተክርስቲያን እያደገች ስትመጣም የሁለቱንም ወገን ስጦታዎችና አገልግሎት ይቀበሉ ጀመር፡፡ በብሉይ ኪዳን ለነበረውም ህዝቡ የገለጠውን የመንግሥቱን ተስፋ ለመፈፀም እግዚአብሔር አህዛብን እንደሚጠቀምም ተረዱ፡፡ ይህም በማያምኑት አይሁድና በቀደሙት ክርስቲያኖች መካከል ወደ በርካታ ግጭቶች ማምራቱ አያስደንቅም፡፡

የሐዋርያትን ሥራ በምናጠናበት ወቅት ሉቃስ የጻፈበትን ወቅት፣ ለየትኞቹ ተደራሲያን እንደጻፈ እና የጻፈበትን ማህበረሰባዊ አውድ አንዳንድ ዝርዝሮች ማወቃችን በእጅጉ ይጠቅመናል፡፡ ሉቃስ ያነሳሳቸውን ችግሮችና የሰጣቸውን መፍትሄዎች ስንረዳ አቀራረቡን ለማድነቅና በተሻለም መንገድ በእኛ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁዎች እንሆናለን፡፡

# 4. ነገረ-መለኮታዊ ዳራ

የሐዋርያትን ሥራ ታሪካዊ መቼትና ጸሐፊውን መርምረናል፣ አሁን ደግሞ የዚህን ርዕስ ሦስተኛ ዐቢይ ነጥብ ማለትም የሐዋርያት ሥራን ነገረ-መለኮታዊው ዳራ ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

የሐዋርያትን ሥራ ስናጠና፣ በርካታ ነገረ-መለኮታዊ ጥያቄዎች ወደ ልቡናችን ይመጣሉ፡፡ ሉቃስ ነገረ-መለኮታዊውን አመለካከት የት ተማረው? በመጽሐፉ ውስጥ ምንን ለመዳሰስ እና ምንስ ላለመንካት ወሰነ? አጻጻፉን ይመራ የነበረው ምን ገዢ መርህ አለ? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱን የምናገኘው በሉቃስ ነገረ-መለኮታዊ ዳራ ውስጥ ይሆናል፡፡

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነገረ-መለኮታዊ ዳራ ላይ የምናደርገው ውይይት በሦስት የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ የሉቃስን ነገረ-መለኮት ብሉይ ኪዳናዊ መሰረቶች እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ነገረ-መለኮቱ ስለ መሲሃዊው የእግዚአብሔር መንግሥት በነበረው እምነት ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳደረበት እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ፣ የሉቃስ ሥራ የመጀመሪያ ቅፅ የሆነው የሉቃስ ወንጌል፣ የሐዋርያት ሥራን መልእክት ከመረዳት አንፃር እንዴት እንደሚያግዘን እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን የሐዋርያት ሥራ ብሉይ ኪዳናዊ መሠረት እንመልከት፡፡

# ብሉይ ኪዳን

ብሉይ ኪዳን የሉቃስን አፃፃፍ ቢያንስ በሁለት መንገዶች ተፅዕኖ አሳድሮበታል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሉቃስ ብሉይ ኪዳን ስለ ታሪክ ባለው አመለካከት በእጅጉ ተነክቷል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በተለይ ስለ እስራኤል ታሪክ ቢያቀርበው ዘገባ በእጅጉ ተፅዕኖ አድሮበታል፡፡ እስኪ አስቀድመን ብሉይ ኪዳን ስለ ታሪክ ያለው ጥቅል አመለካከት እንዴት የሉቃስን ነገረ-መለኮት እንደቀረፀው እንመልከት፡፡

## ታሪክ

በየታሪክ ዘመናቱ የሰው ዘር በእንዴት አይነት መንገድ ይታይ እንደነበረ የ17ኛው ክፍለ ዘመን ክርስቲያን ፈላስፋ የነበረው ብሌይዝ ፓስካል፣ *Penses* በተሰኘው ድንቅ ሥራው ስለ ሦስት ታላላቅ እውነቶች ተናግሯል፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ፍጥረት ውበትና ክብር፣ እግዚአብሔር ሁሉን መልካም ከማድረጉ የተነሳ ፍጥረት ምንኛ ድንቅ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ሁለተኛ፣ በፍጥረት የጅማሬ ክብርና አሁን በሚገኝበት ምስቅልቅልና ርኩሰት መካከል ስላለው ግራ የሚያጋባ ተቃርኖ ጠቅሷል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ፓስካል ስለ ድነት፣ ይህ ተቃርኖ ስለሚጠብቀው የመፍትሄ ተስፋ ይናገራል፡፡

ፓስካል የሰጠው ድምዳሜ ብሉይ ኪዳን ስለ ዓለም ታሪክ ካቀረባቸው ሦስት እርከኖች ጋር ማለትም ከፍጥረት፣ በኃጢአት ከመውደቅና ከድነት ጋር ተጓዳኝ ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ፣ ሉቃስ ስለ መጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ሲፅፍ ስለ ታሪክ ባለው በዚህ የሦስትዮሽ አመለካከት አንፃር ጽፏል፡፡

የፍጥረትን ወቅት እስኪ እንመልከት፡፡ በዘፍጥረት 1፣ ዓለምን የእርሱ ሰማያዊ መንግሥት አካል አድርጎ እግዚአብሔር አዘጋጃት፡፡ ፍጥረተ ዓለሙን በሥርዓት አዋቀረ፤ በዔድን ገነትን ተከለ፤ የእርሱ አምሳያ የሆነውን የሰውን ዘር፣ በገነት ውስጥ አስቀመጠው፤ በገነትም ውስጥ የሰው ዘር እንዲበዛና ምድርን እንዲገዛ፣ ከዔድን በመነሣት እስከ ምድር ዳርቻ ድረስም እንዲሰፋ አዘዘው፡፡ በአጭሩ፣ መንግሥቱ በምድር ላይ በሙላት የምትገለጥበትን መድረክ እግዚአብሔር አዘጋጀ፡፡

ሉቃስ ስለዚህ የብሉይ ኪዳን ወሳኝ እሳቤ ያለው ግንዛቤ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በበርካታ ስፍራዎች ይታያል፡፡ ለአብነት ያህል፣ በ4፡24-30 ውስጥ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ ስለ መሆኑ ፍጥረትን ዋቢ አድርገው ተናግረዋል፡፡ በ14፡15-17 ውስጥ፣ ጳውሎስና በርናባስ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ገዢ የመሆኑ መሠረት አድርገው ስለ ፍጥረት ተናግረዋል፡፡ በ7፡49 ውስጥ፣ እስጢፋኖስ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው ንጉሣዊ የእግሩ

ማረፊያ እንዲሆንለት እንደሆነ ጠቅለል አድርጎ ጠቅሷል፡፡ በሐዋርያት ሥራ 17፡24-27 ውስጥ ጳውሎስ በአቴንስ የተናገረውን አድምጡ፡

***ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤***
***እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።***
***ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም።(የሐሥ 17፡24-27)***

በዚህ ምንባብ መሠረት፣ የጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት ፍጥረትን ሁሉ ዳሷል፡፡ እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ የፈጠረ ጌታ ነው፡፡ እርሱ ዓለምን በስርዓት አዋቀረ ስለዚህም ሰዎች እርሱን ይሻሉ፣ ወደ እርሱም ይናፍቃሉ ያገኙታልም፡፡ የጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት እግአብሔር በመፍጠር ወቅት ካስቀመጠው ዓላማ ውስጥ የወጣ ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ እነዚህን ዝርዝሮች በማካተት፣ የቀደመችውን ቤተክርስቲያን ከመረዳት አንፃር የፍጥረት መሪ ሃሳብ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ሉቃስ አመልክቷል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ ሉቃስ ስለ ሰው ዘር በኃጢአት መውደቅ ያለው መረዳት በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በጉልህ ተቀምጧል፡፡ እንደምናውቀው፣ ዘፍጥረት 3 እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር የሰውን ዘር ከፈጠረ በኋላ፣ አዳምና ሔዋን በእርሱ ላይ አመፁ፡፡ የዚህም ተፅዕኖ የከፋ ነበር፡፡ እንደ ብሉይ ኪዳን አገላለፅ፣ የሰው ዘር በዓለም ላይ ቁልፍ ሚና ያለወ በመሆኑ በኃጢአት መውደቁ የሰውን ዘር በጠቅላላ በሞት እርግማን ስር የጣለው ሲሆን ፍጥረትን በጠቅላላ አረከሰ፡፡

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሉቃስ የኃጢአትን አሰቃቂ ገፅታ በበርካታ ስፍራዎች ጽፎታል፡፡ ጴጥሮስ በ2፡38 እና በ3፡19 ውስጥ በሰበካቸው ስብከቶች፣ በ5፡29-32 ሐዋርያት በሸንጎው ፊት ባቀረቡት መከራከሪያ፣ በ20፡18-35 ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ባደረገው ንግግር እና በ26፡20 በንጉሥ አግሪጳ ፊት ጳውሎስ ባደረጋቸው ንግግሮች ውስጥ የዚህን ውድቀት ማስረጃዎች እናገኛለን፡፡

በፍጥረት ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ፣ ቁሳዊው ዓለም፣ የኤኮኖሚው መዋቅር፣ የፖለቲካ ሥርዓታችን እና ቤተክርስቲያን ራሷም የሰው ዘር በኃጢአት በመውደቁ ምክንያት በጭንቅ ውስጥ እንደሆኑ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደጋግሞ አመልክቷል፡፡

ደስ የሚያሰኘው ነገር፣ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ የዘገበው ታሪክ ስለ ፍጥትና ውድቀት በብሉይ የተዘገበውን ብቻ ሳይሆን፣ ብሉይ ስለ መቤዠት የሚናገረውንም ያካተተና በዚያም ያለውን እምነት የዘገበ መሆኑ ነው፡፡ ኃጢአት እጅግ የከፋና ሰውንና ፍጥረትን ሁሉ የመበከሉን ያህል፣ እግዚአብሔር ግን ፍጥረትን ያለ ተስፋ እንዳልተወ ሉቃስ ያምናል፡፡

ኃጢአት ገና በመጀመሪያው ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር ሰዎችን ከኃጢአት እርግማን ሲያድንና ሲዋጅ እንደነበረ ብሉይ ኪዳን ያስተምረናል፡፡ ከዚህም በበለጠ፣ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ኃጢአትና እርግማን ለዘላለም ከፍጥረት ላይ የሚወገዱበትን ቀን ይተነብዩ ነበር፡፡ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ሲጽፍ፣ ይህ መቤዠት ወደ ዓለም የሚመጣው በክርስቶስ የማዳን ሥራ አማካይነት መሆኑን እንደሚያምን ደጋግሞ አመልክቷል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ይታያል፡፡

ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፣ እነዚህን የትድግና መሪ ሃሳቦች፡ በ2፡21-40 በጴጥሮስ ስብከት ውስጥ፤ በ5፡29-32 ሐዋርያት በሸንጎው ፊት ባቀረቡት መከራከሪያ፤ በ11፡14 መልዓኩ ለቆርኔሌዎስ በተናገረው ንግግር ውስጥ፤ በ13፡23 ጳውሎስ በጵስድያዋ አንጾኪያ ጳውሎስ በምኩራብ ባደረገው ንግግር፤ በ15፡7-11 ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ጉባዔ ፊት ባቀረበው ሙግት እና በ16፡30-31 ጳውሎስና ሲላስ ለወህኒው ሃላፊ በተናገሩት ንግግር ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡

የሐዋርት ሥራ መጽሐፍን ስንቀርበው፣ ሉቃስ በሚጽፍበት ወቅት ብሉይ ኪዳን ስለ ዓለም ታሪክ ባለው አመለካከት በእጅጉ ተፅዕኖ ያደረበት መሆኑን ልብ ማለት ይገባናል፡፡ ስዚህም በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩት ክስተቶች ከፍጥረት ጀምሮ ያለውን የዓለም ታሪክ፣ በኃጢአት መውደቅንና ቤዠዎት በክርስቶስ መሆኑን የሚያመለክቱ መሆናቸውን በመግለፅ ደጋግሞ ዘግቧል፡፡

ብሉይ ኪዳን ስለ ታሪክ ያለውን ራዕይ በጥቅሉ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በተለይ ስለ እስራኤል ታሪክ ያለውን ራእይ እና ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ያቀረበው ዘገባ በዚህች ልዩ ሀገር ጣሪክ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

## እስራኤል

ሉቃስ የሐዋርያትን ሥራ ሲጽፍ በእስራኤል ታሪክ ላይ ተደገፈባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ለውይይታችን ያህል፣ ነገራችንን በእስራኤል ታሪክ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ እንገድበዋለን፡፡ እነርሱም፡ እግዚአብሔር አብርሃምን መምረጡ፣ ዘፀአት በሙሴ አመራር እና የዳዊት ስረወ-መንግሥት መመሥረት ናቸው፡፡ በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር አብርሃምን መምረጡ የሉቃስን ታሪክ እንዴት እንደ ቀረፀው እንመልከት፡፡

ዘፍጥረት 12፡1-3 እግዚአብሔር አብርሃምን የአንድ ልዩ መንግሥት አባት አድርጎ መምረጡን ዘግቧል፡፡ እንዲህ ይነበባል፡

> **እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።**
> **ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን**
> **የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ። (ዘፍ 12፡1-3)**

በነዚህ ጥቅሶች አገላለጥ፣ ለሁለት  ዐቢይ ዓላማዎች ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲሄድ እግዚአብሔር አብርሃምን ጠራው፡፡

በአንድ በኩል፣ አብርሃም የአንድ ትልቅ ህዝብ አባት፣ ታዋቂ እና በርካታ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ በረከቶችን ይቀበላል፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ከእርሱም በኋላ ለዘሩ የሰጠው በረከት፣ በዚህ በወደቀው ዓለም ውስጥ እንኳን የእግዚአብሔር የድነት ተስፋ መኖሩን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ጥሪ አብርሃምና ዘሩ ከሚቀበለውም በረከት እጅግ ተሻግሮ ይሄዳል፡፡ በአብርሃም አማካይነት፣ በምድር ያለ ህዝብ ሁሉ ይባረካል፡፡ አብርሃምና ዘሩ በምድር ለሚኖሩ ህዝቦች ሁሉ የመለኮታዊ በረከት መተላለፊያ ይሆናሉ፡፡

እግዚአብሔር አብርሃምን የመረጠበት ይህ መንታ ትኩረት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ የነበረውን አስተሳሰብ ያሰምርበታል፡፡ በአንድ ወገን፣ በክርስቶስ የተገኘው የድነት በረከት የአብርሃም ወገን ወደሆኑት አይሁድ እንዴት እንደደረሰ እና ለታላላቅ አባቶች የእግዚአብሔር ተስፋ እንዴት እንደተፈፀመ ደጋግሞ ዘግቧል፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ፣ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች የክርስቶስን ወንጌል እንዴት ወደ አህዛብ እንዳደረሱ ሉቃስ ትኩረት አድርጓል፡፡ ከጊዜ በኋላ ደግሞ፣ ፊሊጶስ፣ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ እና በርናባስን የመሳሰሉት አይሁዳውያን የድነትን ወንጌል ወደ አህዛቡ ዓለም እንዳደረሱ ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ተስፋ ፈጽሟል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ያንጸባረቀው አመለካከት በሙሴና በክርስቲያን ቤተክርስቲያን መካከል ስላለው ግንኙነት ያለውን ግንዛቤ ያመለክታል፡፡ ሙሴ እንደ እግዚአብሔር ነፃ አውጪ፣ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት አወጣ፣ ለህዝቡም የእግዚአብሔርን ህግጋት ሰጠ ለህጉም ተጠያቂ እንዲሆኑ አደረገ፡፡ በዚያው ህግ፣ እግዚአብሔር እንደ እርሱ ያለ ነቢይ አንድ ቀን እንደሚልክና ህዝቡንም ከኃጢአት ባርነት ነፃ እንደሚያወጣ ሙሴ ተንብዮአል፡፡ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንዳመለከተው፣ ይህ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ኢየሱስ ሆነ፡፡ በሐዋርያት ሥራ 7፡36-39 እስጢፋኖስ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***ይህ ሰው በግብፅ ምድርና በኤርትራ ባሕር በምድረ በዳም አርባ ዓመት ድንቅና ምልክት እያደረገ አወጣቸው።***
> ***ይህ ሰው ለእስራኤል ልጆች። እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል፤ እርሱን ስሙት ያላቸው ሙሴ ነው።***
> ***ይህ ሰው በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማኅበሩ ውስጥ የነበረው ነው፤ ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ፤***
> ***ለእርሱም አባቶቻችን ሊታዘዙት አልወደዱም፤ ነገር ግን ገፉት በልባቸውም ወደ ግብፅ ተመለሱ፤ (ሐሥ 7፡36-39)***

ከእስጢፋኖስ አመለካከት አንፃር፣ ኢየሱስ ሙሴ አስቀድሞ የተነበየለት ነቢይ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስን ማቃለል ማለት ልክ የቀደሙት እስራኤላውያን እንዳደረጉት ሙሴንና ህጉን ማቃለል ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በእውነት ለሙሴና ለህጉ የተሰጠ ከሆነ፣ ክርስቶስን መቀበል አለበት፡፡

በሐዋርያት ሥራ 28፡23 ጳውሎስ ለአይሁድ መሪዎች ያደረገውን ንግግር ሉቃስ እንዴት ጠቅለል እንዳደረገው እንመልከት፡

***ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም እየመሰከረ ስለ ኢየሱስም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት ጠቅሶ እያስረዳቸው፥ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ይገልጥላቸው ነበር። (የሐሥ 28፡23)***

ለጳውሎስና ለቀደመችው ቤተክርስቲያን በጠቅላላ፣ ሙሴንና ህጉን የመቀበሉ ነገር በክርስቶስ ላለው እምነት መሠረታዊ ነው፡፡ ይህም እምነት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ በጻፈው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ፣ ብሉይ ኪዳን ስለ ዳዊት ስርወ-መንግሥት የዘገበው ሉቃስን ተፅዕኖ አሳድሮበታል፡፡ ለሉቃስ የዳዊት ቤት በእስራኤል የማይፈርስ ስርወ-መንግሥት ሆኖ ከመመሥረቱ የሚበልጥ ሌላ መሪ ሃሳብ አለ ብሎ ለማሰብ እንኳን የማይቻል የሆነበት ይመስላል፡፡

በብሉይ ኪዳን እስራኤል ወደ መንግሥትነት ስታድግ፣ እግዚአብሔር ህዝቡን ይመራለት ዘንድ የዳዊትን ቤት ቋሚ መንግሥት እንዲሆን መረጠ፡፡ በተጨማሪም የዳዊት ቤት ግዛቱን በማስፋት የእግዚአብሔር አገዛዝ ከእስራኤል አልፎ ምድርና ሞላዋን የሚሸፍን መሆኑንም ብሉይ ኪዳን አመልክቷል፡፡

በመዝሙር 72፡8፣17 እንዲህ ይነበባል፡

***ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፥ ከወንዝም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል። …***

***ስሙ ለዘላለም ቡሩክ ይሆናል፥ ከፀሐይም አስቀድሞ ስሙ ይኖራል የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉም አሕዛብ ሁሉ ያመሰግኑታል። (መዝ 72፡8፣17)***

እነዚህ ጥቅሶች እንደገለጡት፣ አብርሃም ለምድር ሁሉ በረከት የሚሆነው በዘሩ በዳዊት በኩል ነው፡፡ ዳዊት ግን ይህንን በራሱ አልፈፀመውም፡፡ ይልቁኑ፣ ከዘሮቹ አንዱ የእርሱን በጎና ቅን፣ ሰላም የሞላበት አገዛዝ በመላው ዓለም ለማምጣት ይነግሣል፡፡

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ሉቃስ ይህንን ተስፋ ከዳዊት ቤት ውስጥ በጥልቀት አውጥቶታል፡፡ ኢየሱስ የዳዊት ልጅ፣ በቤተክርስቲያንም አማካይነት ከኢየሩሳሌም አንስቶ እስከ ምድር ዳር ድረስ አገዛዙን የሚያሰፋ የእግዚአብሔር መንግሥት ንጉሣዊ ገዢ መሆኑን ተረድቷል፡፡

ለምሳሌ፣ በሐሥ 15፡14-18 ውስጥ ያዕቆብ ለኢየሩሳሌም ጉባዔ የተናገረውን አድምጡ፡

***እግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን ተርኮአል።***
***ከዚህም ጋር የነቢያት ቃል ይሰማማል፥ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ።***
***ከዚህ በኋላ የቀሩት ሰዎችና በስሜ የተጠሩት አሕዛብ ሁሉ ጌታን ይፈልጉ ዘንድ እመለሳለሁ፥ የወደቀችውንም የዳዊትን ድንኳን እንደ ገና እሠራታለሁ፥ ፍራሽዋንም እንደ ገና እሠራታለሁ እንደ ገናም አቆማታለሁ ይላል ይህን የሚያደርግ ጌታ።***
***ከጥንት ጀምሮ ሥራው ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው።***
***(የሐሥ 15፡14-18)***

በዚህ ስፍራ ያዕቆብ የጠቀሰው ከአሞጽ 9፡11-12 ሲሆን፣ በዚያም እግዚአብሔር የዳዊትን ዙፋን እንደገና በማፅናት መንግሥቱን በአህዛብ መንግሥታት ላይ እንደሚያሰፋ አሞጽ ተንብዮአል፡፡ በዚህ ስፍራ፣ ወንጌል ወደ አህዛብ ሁሉ የደረሰው የእነዚህ የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ፍፃሜ በመሆነ መሆኑን ያዕቆብ ያምናል፡፡

ኢየሱስ ለአብርሃም የተነገሩ ተስፋዎች ወራሽ፣ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ እና የመጨረሻው ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ መሆኑን አንባቢዎቹ እንዲረዱለት ሉቃስ ይፈልጋል፡፡ በወንጌሉ መታወጅና እና በቤተክርስቲያን እድገት፣ ከኢየሩሳሌም አንስቶ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ የማዳኑን መንግሥት በማስፋት፣ በብሉይ ኪዳን እንደተተነበየው ኢየሱስ መንበረ ንግሥናውን ይዟል ዓለምን ድል አድርጓል፡፡

# የእግዚአብሔር መንግሥት

ሉቃስ በብሉይ ኪዳን ላይ ያለውን መደገፍ ከተመለከትን፣ የእግዚአብሔር መሲሃዊ መንግሥት ለሐዋርያት ሥራ ነገረ-መለኮታዊ ዳራ እንዴት አስተዋፅዖ እንዳበረከተ እንመለከታለን፡፡

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምናደርገው ውይይት በሦስት የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ በአንደኛው ክፍለ ዘመን በስፋት የነበረውን የአይሁድ መሲሃዊ ነገረ-መለኮት እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ በመጥምቁ ዮሐንስ ነገረ-መለኮት ላይ እናተኩራለን፡፡ ሦስተኛ፣ ሉቃስ ከተቀበለው የክርስቲያን መሲሃዊ ነገረ-መለኮት ጋር እነዚህን አመለካከቶች እናነፃፅራቸዋለን፡፡ በአይሁድ ነገረ-መለኮታዊ አስተሳሰብ እንጀምር፡፡

## የአይሁድ ነገረ-መለኮት

በአምስተኛው ዓ.ዓ. የመጨረሻዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከተጻፉ በኋላ፣ እስራኤል በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ወደቀች፡፡ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት፣ አብዛኞቹ እስራኤላውያን ከተስፋይቱ ምድር ውጪ ይኖሩ ነበር፣ በምድሪቱ ውስጥ የቆዩትም በአህዛብ መሪዎች ጭቆና ስር ይማቅቁ ነበር፡፡ በመጀመሪ ባቢሎናውያን፣ ከዚያም ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክ በመጨረሻም ሮማውያን ነበሩ፡፡ ለረጅም ዘመናት ከዘለቀው ከዚህ የጭቆና ታሪክ የተነሣ፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ የሚወጣ መሲህ የመላኩ ተስፋ በአይሁድ ነገረ-መለኮት ውስጥ ሁሉን የሚገዛ አንቀሳቃሽ ኃይል ሆነ፡፡

የአይሁድ መሲሃዊ ተስፋዎች የተለያዩ በርካታ አቅጣጫዎችን ያዙ፡፡ ለምሳሌ፣ ቀናተኞች ይባሉ የነበሩት በመሲሁ ዘመን በሮማውያን ላይ ሁከትን ለማስነሳት እግዚአብሔር እስራኤልን ይጠቀማል ብለው ያምናሉ፡፡ የተለያዩ አቡቀለምሲሳዊ ቡድኖች እግዚአብሔር ጠላቶቹን ለማጥፋት እና ሕዝቡንም ድል አድራጊ አድርጎ ለመመሥረት በመለኮታዊ ጉልበቱ ጣልቃ ይገባል ብለው ያምናሉ፡፡ በተጨማሪም ታዋቂ የሆኑ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ደግሞ እስራኤል ህጉን እስካልታዘዘች ድረስ እግዚአብሔር ጣልቃ አይገባም ብለው ያምኑ ነበር፡፡ ሉቃስ በፓለስታይን ምድር ከአይሁድ የነገረ-መለኮት ምሁራን ጋር በርካታ አመታትን በማሳለፉ ስለ እነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች ጥሩ እውቀት ነበረው፡፡ በሐዋርያት ሥራ የተለያዩ ነጥቦች ውስጥ፣ ክርስቲያኖች ስለ መሲሁ መንግሥት ያላቸውን አመለካከት በርካታ አይሁድ ይቃወሙ እንደነበር ሉቃስ ጠቅሷል፡፡

ምንም እንኳን አይሁድ ስለ መሲሁ በርካታ ተስፋዎች ቢኖሯቸውም፣ በአይሁድ ነገረ-መለኮት ውስጥ ወሳኝ የሆነ ለውጥ የመጣው በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ውስጥ መሆኑን አስተውሏል፡፡

## መጥምቁ ዮሐንስ

የሉቃስ ወንጌልም ሆነ የሐዋርያት ሥራ መጥምቁ ዮሐንስ የእውነተኛ ንስሓ ጥሪ ያቀርብ እንደነበር እና መሲሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር እንደሚያመጣ የሚናገረውን መልካሙን የምሥራች ያውጅ እንደነበር አመልክተዋል፡፡ ከዚህም በበለጠ፣ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን በቀጥታ አመልክቷል፡፡ በሉቃስ 3፡16-17 መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***በሰሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው። አሁንም፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁ፤ (ሉቃስ 3፡16-17)***

በዚህ ስፍራ መሲሁ ታላቅ በረከትን፣ በመንፈስ ቅዱስ የሆነውን ማንፃት ፍርድንም ጨምሮ እንደሚያመጣ ዮሐንስ በቀጥታ አመልክቷል፡፡ ሆኖም ግን መሲሁ ይህንን ሁሉ በአንድ ጊዜ ያከናውናል በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ ነበር፡፡

ዮሐንስ መሲሁ ድነትንና ፍርድን በዓለም ላይ በየደረጃው እንደሚያመጣ አላየም ነበር፡፡ ቆየት ብሎ፣ የአይሁድ የነገረ-መለኮት ምሁራን መሲሁ ያከናውናል ብለው የሚጠብቁትን ሁሉ ኢየሱስ ገና እንዳልፈፀመ ሲመለከት ዮሐንስ ግራ ተጋብቶ ነበር፡፡ ኢየሱስ በእውነት መሲሁ መሆን አለመሆኑን እንዲጠይቁለት ሰዎችን እስኪልክ ድረስ ተቸግሮ ነበር፡፡

በሉቃስ 7፡20-23 ጥያቄያቸውንና ኢየሱስ የሰጣቸውን ምላሽ ሉቃስ የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***ሰዎቹም ወደ እርሱ መጥተው። መጥምቁ ዮሐንስ። የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ? ብሎ ወደ አንተ ላከን አሉት።***
> ***በዚያች ሰዓት ከደዌና ከሥቃይ ከክፉዎች መናፍስትም ብዙዎችን ፈወሰ፥ ለብዙ ዕውሮችም ማየትን ሰጠ።***
> ***ኢየሱስም መልሶ፦ ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ፥ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ፥ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ፥ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤***
> ***በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው አላቸው። (ሉቃስ 7፡20-23)***

ኢየሱስ ለመጥምቁ ዮሐንስ በሰጠው ምላሽ፣ በኢሳያስ መጽሐፍ የተጠቀሱ በርካታ መሲሃዊ ትንቢቶችን ጠቅሷል፡፡ ምንም እንኳን ሁሉንም ገና ያልፈፀማቸው ቢሆንም ብሉይ ኪዳን ያስቀመጣቸውን መሲሃዊ ትንቢቶች በመፈፀም ሂደት ላይ መሆኑን ለዮሐንስ ሊያረጋግጥለት ፈልጓል፡፡ መሲሃዊ ሥራው ገና ያልተገለጠ በመሆኑ ምክንያት እንዳይሰናከል ኢየሱስ ዮሐንስን አበረታትቶታል፡፡

በአጭሩ፣ የኢየሱስ መሲሃዊ ተልዕኮ ከሚጠበቀው እጅግ የተለየ ይመስላል፡፡ የአይሁድ መሲሃዊ ተስፋዎች ከጥቂት ዓመታት በፊት ልክ ዳዊት እንደመራበት ዓይነት ያለ ፖለቲካዊ መንግሥት አሁኑኑ ይመሠርታል ብለው ይጠብቁ ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን በምድራዊ አገልግሎቱ ይህንን የመሰለውን መንግሥት አልመሠረተም፡፡

የአይሁድን መሲሃዊ ነገረ-መለኮትና መጥምቁ ዮሐንስ በልቡናው ይዞት የነበረውን አመለካከት በዚህ መንገድ ከተረዳን፣ ስለ መሲሁና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቀደምቱ የክርስቲያን ነገረ-መለኮት ወደሚናገረው እንሸጋገራለን፡፡

## የክርስቲያን ነገረ-መለኮት

እንደተቀሩት የአዲስ ኪዳን ጽሁፎች ሁሉ፣ በሉቃስ ጽሑፎችም ውስጥ፣ ክርስቲያናዊው ነገረ-መለኮት ከክርስቲያን ወንጌል ወይም መልካም የምሥራች ጋር በበብርቱ የተቆራኘ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳኑን የወንጌል መልእክት በዚህ መንገድ ጠቅለል ማድረግ እንችላለን፡

> ***ወንጌል የእግዚአብሔር መንግሥት በኢየሱስ፣ በመሲሁ ማንነትና ሥራ ወደ ምድር የመምጣቷ እና ኢየሱስን እንደ መሲህ ለሚቀበሉና ለሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጠው ድነት የሚሰፋ አዋጅ ነው፡፡***

የወንጌል መልእክት በሁለት መሠረታዊ ሃሳቦች ላይ ያረፈ መሆኑን ታስተውላላችሁ፡፡ በአንድ በኩል፣ በክርስቲያን ወንጌል ውስጥ ተጨባጭ የሆነውን ጉኑን እናገኛለን፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኢየሱስ ማንነትና ሥራ ወደ ምድር መጥታለች፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር የመምጣቷን የፍፃሜ እርከን ኢየሱስ እንደ መሲህ መጀመሩን እና አንድ ቀንም የጀመረውን ለመፈፀም እንደሚመለስ ሉቃስ ያምናል፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ፣ የአዲስ ኪዳን የወንጌል መልዕክት ከሁኔታዎች ጋርም የተያያዘ ጎን አለው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የመጨረሻው እርከን ኢየሱስን እንደመሲህ ለሚቀበሉና ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ድነትን እስከሚሰጥበት እስከታላቁ የሙላት ቀን ድረስ እንደሚዘልቅ ያውጃል፡፡ ወንጌል ያመኑትን ሰዎች ልብ ሲነካና ኢየሱስ ወደ ፈፀመው ድነት ሲያመጣቸው እግዚአብሔር ዓለምን የመግዛቱ እውነት እየሰፋ ይሄዳል፡፡

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ሉቃስ ወደ እነዚህ ሁለት የወንጌል አድማሶች ትኩረትን ይስባል፡፡ በመሠረታዊ ጭብጥ ጎኑ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ባከናወነው የድነት ሥራ እውነታዎች ላይ ያተኩራል፡፡ ኢየሱስ ስለ ህዝቡ ኃጢአት መሞቱን፣ ከሞት መነሣቱን፣ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ መቀመጡንና አንድ ቀንም በክብር መመለሱን የሚተርከውን የቤተክርስቲያን አዋጅ ዘግቧል፡፡

ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ 2፡22-24 በጰንጠቆስጤ ዕለት ጴጥሮስ የሰበከውን ስብከት አድምጡ፡

> ***የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤***
> ***እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት።***
> ***እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና። (የሐሥ 2፡22-24)***

የጴጥሮስ የወንጌል አወጃ የኢየሱስን ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ጭብጥ ጎኖች ያካተተ መሆኑነ ልብ በሉ፡፡

ሉቃስ በተጨማሪም ከሁኔታዎች ጋር ወደ ሚያያዘውም የወንጌል ጎን ትኩረት ያደርጋል፡፡ ሰዎች ሕይወታቸው ይለወጥ ዘንድ የክርስቶስን እውነት በግላቸው መቀበል አስፈላጊ መሆኑንም ጫን በማለት ያሳያል፡፡

ለምሳሌ፣ በሐሥ 2፡37-39 ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ዕለት ያደረገው ንግግር እነዚህን ቃላትም አካትቷል፡

> ***ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው።***
> ***ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።***
> ***የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። (የሐሥ 2፡37-39)***

የክርስትና ወንጌል የሚሰሙትን ሰዎች ልብ ሰንጥቆ ገባ፡፡ ነገሩ ለእውነታ እውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን አይደለም ይልቁኑ ከልብ በመነጨ፣ ሕይወትንም በሚለውጥ መንገድ ከአዳኙ ጋር መገናኘት ነው፡፡

ቀደም ብለን እንደተናገርነው የመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የአይሁድ ነገረ-መለኮት መሲሁ በአንድ ጊዜ ፖለቲካዊውን መንግሥት ይመሠርታል ብሎ ያምናል፡፡ ኢየሱስና ሐዋርያቱ ያስተማሩት ግን የመሲሁ መንግሥት በቤተክርስቲያን መስፋፋትና በሰዎችም ግላዊ የሕይወት ለውጥ አማካይነት ቀስ በቀስ እያደገ እንደሚመጣ ነው፡፡

ወንጌል በሚሰበክበት ወቅት ያላመኑት ስለሚለወጡበት ሁኔታ ሉቃስ ጠንካራ አጽንኦት የሰጠበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መሲሃዊ መንግሥት በመላው ዓለም የሚሰፋበት መንገድ ይህ እንደሆነ ያውቃል፡፡

ይህን የብሉይ ኪዳን ራዕይ ሰፊ ዳሰሳ በልቡናችን ይዘን፣ የሐዋርያት ሥራን ዳራ ሦስተኛ ነገረ-መለኮታዊ ገፅታ እንመረምራለን፡፡ ያም በሉቃስ ወንጌል ያለውን መሠረት ነው፡፡

# የሉቃስ ወንጌል

የሐዋርያት ሥራን ስናነብብ፣ ሉቃስ ለቴዎፍሎስ የጻፈው ባለሁለት ቅፅ ታሪክ ሁለተኛው መሆኑን ማስታወስ ይገባናል፡፡ ሉቃስ እነዚህ መጻሕፍት በአንድነት እንዲነበቡ ይፈልጋል፡፡ ወንጌሉ የታሪኩ የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን የሐዋርያት ሥራ ደግሞየታሪኩ ሁለተኛ ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ የሐዋርያት ሥራን በትክክል ለማንበብ፣ በወንጌሉ የተጀመረው ታሪክ እንዴት እንደቀጠለ ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

የሉቃስ ወንጌል የሐዋርያት ሥራን መልእክት ከመረዳት አንፃር ዝግጁ እንድንሆን የሚያደርግባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ለአሁኑ ዓላማችን ግን በሁለቱም ቅጾች በዘለቀው የእግዚአብሔር መንግሥት መሪ ሃሳብ ላይ እናተኩራለን፡፡ በሉቃስ ወንጌል፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ንድፍና ግብ ያስቀመጠ ሲሆን ከእርገቱ በኋላ በእርሱ የተጀመረውን ሥራ እንዲቀጥሉ ሐዋርያቱን አዘጋጅቷቸዋል፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ በመንፈስ ቅዱስ በመታገዝ በወንጌል አማካይነት መንግሥቱን እንዲያሰፉ በመንገር ሐዋርያቱን ተለይቶ ኢየሱስ ወደ ሰማይ አርጓል፡፡ በሐዋርያት ሥራ እንደተገለጠው ሐዋርያቱ የመንግሥቱን ግንባታ ሥራ ለሚቀጥሉበት አገልግሎት የሉቃስ ወንጌል መንገዱን እንዴት እንደሚጠርግ በሁለት መንገዶች እናያለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መንግሥቱን ያመጣውን ኢየሱስን እናያለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ኢየሱስ ወደ ሰማይ

ካረገ በኋላ፣ ሐዋርያት መንግሥቱን የማምጣቱን ሥራ የመቀጠል ድርሻቸውን እንመረምራለን፡፡ መንግሥቱን ባመጣው በኢየሱስ እንጀምር፡፡

## ኢየሱስ

ሉቃስ በወንጌሉ በጠቅላላ፣ ኢየሱስን የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት እንደሚያውጅ ነቢይ፣ ወደ ዙፋንም በመውጣት መንግሥቱን እንደሚያጸና ንጉሥ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ ኢየሱስ ራሱም በበርካታ ስፍራዎች ስለእነዚህ ስለ ሁለቱም ነገሮች ተናግሯል፡፡ አሁን ለምንጠቀምበት መግለጫ ያህል ግን በአደባባይ አገልግሎቱ ወቅት የጠቀሳቸውን ሁለት ጊዜያት ብቻ እንጠቅሳለን፡፡

በአንድ ወገን፣ በሉቃስ 4፡43 ውስጥ፣ በአደባባይ አገልግሎቱ ጅማሬ አቅራቢያ እንዲህ ተናግሯል፡

> ***እርሱ ግን፡- ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው። (ሉቃስ 4፡43)***

በሌላ ወገን ደግሞ፣ በአደባባይ አገልግሎቱ ፍጻሜ አካባቢ፣ ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ንጉሥ ሊገባ ባለበት ወቅት፣ በሉቃስ 19፡12-27 ኢየሱስ ስለ ዐሥሩ ምናን ምሳሌ ተናገረ፡፡ በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ መንግሥቱ በእንዴት አይነት መንገድ ቀስ በቀስ እንደምትመጣ አብራርቷል፡፡ በእርሱ ዘመን የነበሩ አብዛኞቹ አይሁድ መንግሥቱ በሙላት ወዲያውኑ ትመጣለች ብለው ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን መንግሥቱን የሚያመጣው ቀስ በቀስና ደረጃ በደረጃ መሆኑን አስተምሯል፡፡ ኢየሱስ መንግሥቱን ጀምሯል፣ ሁሉን አጠናቅቆ ዘውድ የጫነ ንጉሥ ሆኖ ለመገለጥ ግን ወደ ሰማይ ሄዷል ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ መንግሥቱ አትጠናቀቅም፡፡

በሉቃስ 19፡11-12 የምናኑ ምሳሌ እንዴት እንደሚጀምር አድምጡ፡

> ***እነርሱም ይህን ሲሰሙ፥ ወደ ኢየሩሳሌም መቅረቡ ስለ ሆነ የእግዚአብሔርም መንግሥት ፈጥኖ ሊገለጥ እንዳለው ስለ መሰላቸው ምሳሌ ጭምር ተናገረ። ስለዚህም እንዲህ አላቸው፡- አንድ መኰንን ለራሱ መንግሥትን ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ አገር ሄደ። (ሉቃስ 19፡11-12)***

በዚህ ስፍራ የሆነውን ልብ በሉ፡፡ ኢየሩሳሌም ወደ ኢየሩሳሌም ሊገባ ተቃርቧል ደግሞም ንጉሥ ተብሎም ታውጆለታል፣ እርሱ ግን በዚህ ወቅት ምድራዊ ንጉሥ ይሆነናል ብለው ሰዎች እንዳይጠብቁ ይፈልጋል፡፡ ይልቁኑ፣ ንጉሥነቱን ሊቀበል ለረጅም ዘመን ይሄዳል፣ ከዚያም ወደፊት በምድርም ላይ ሊገዛ ተመልሶ ይመጣል፡፡

በኢየሩሳሌም የሆነውም ይኸው ነው፡፡ በኢሩሳሌም፣ ኢየሱስ ተያዘ ተሰቀለም፡፡ ከሞትም ተነሣ፣ ወደ ሰማይም አረገ፣ በዚህም ከአብ ዘንድ ንግሥናውን ተቀበለ፡፡ መንግሥቱን ወደ ሙላት ለማምጣት ተመልሶ ይመጣል፡፡

የሉቃስ ወንጌል ኢየሱስ መንግሥቱን የሚያመጣ አድርጎ ያስቀመጠበትን በዚህ መንገድ ከተረዳን፣ በወንጌሉ ወደተቀመጠው ሁለተኛ ጉዳይ ማለትም፣ በወንጌል አማካይነት ሐዋርያት መንግሥቱን ለማስፋት ስለተሰጣቸው ሃላፊነት ወደ መነጋገሩ እንሸጋገር፡፡

## ሐዋርያት

ኢየሱስ ከተሰቀለባት ቀን በፊት በነበረችው ምሽት፣ መንግሥቱን የማምጣት ሥራውን እንዲቀጥሉ ሐዋርያቱን አዟቸዋል፡፡

በሉቃስ 22፡29-30 የተናገረውን አድምጡ፡

***አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ፥ በአሥራ ሁለቱ በእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ። (ሉቃስ 22፡29-30)***

በመንግሥቱ ውስጥ መሪዎችና ገዢዎች ይሆኑ ዘንድ ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሾሟቸዋል፡፡ ሥራቸውም፣ በመንፈስ ቅዱስ በመታመን፣ የመንግሥቱን ወንጌል ማወጅና ዓለምን ሁሉ እስኪሸፍን ድረስ መንግሥቱን ማስፋት ነበር፡፡

እንግዲያው፣ መንግሥቱን በይፋ ማወጅ የኢየሱስ ተቀዳሚ ሥራ እንደነበረና እርሱ ወደ ሰማይ ካረገም በኋላ ሐዋርያት ያንኑ ሃላፊነት እንዲቀጥሉ ሐዋርያቱን መላክ እንደነበር መግለጥ የሉቃስ ወንጌል ዓላማ ነበር ማለት ነው፡፡

የሐዋርያት ሥራም የሚጀምረው የሉቃስ ወንጌል ካቆመበት ነው፡፡ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላወደ ሰማይ ከማረጉ አስቀድሞ፣ ሐዋርያቱን ለማስተማር አብሯቸው እንዳሳለፈ በመናገር ይጀምራል፡፡

በሐሥ1፡3-8 ሉቃስ የጻፈውን አድምጡ፡

***ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።
ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን። ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤
ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ።
እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት።
እርሱም፡- አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤
ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (የሐሥ 1፡3-8)***

ተከታዮቹ መንግሥቱ አሁኑኑ በሙላት ትመጣለች ብለው እንዳይጠብቁ ኢየሱስ አንድ ጊዜ በድጋሚ በመንገር አበረታቷቸዋል፡፡ ይልቁኑ፣ ወንጌልን በዓለም ሁሉ በማወጅ እርሱ የጀመረውን ሥራ መቀጠል ሃላፊነታቸው መሆኑን ለሐዋርያት አሳስቧቸዋል፡፡

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም ሐዋርያት ያደረጉት ይህንኑ መሆኑን እናነባለን፡፡ የወቅቱ የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ የሆነችውን ቤተክርስቲያንን መሠረቱ፡፡ የመንግሥቱንም ወንጌል ወደ አዳዲስ ምድሮችና ህዝቦች በማድረስ፣ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማርያና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መንግሥቱን አሰፉ፡፡

በሐሥ 28፡30-31 ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን እንዴት እንዳጠቃለለው አድምጡ፡

> ***ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፤***
> ***ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር። (የሐሥ 28፡30-31)***

ሉቃስ በቀላሉ ጳውሎስ "ወንጌል" ሰበከ ከማለት ይልቅ፣ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰበከ ይላል፡፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጠናቀቀው ገና ሲጀምር ነው፣ ይህም ወንጌሉን በማወጅ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ ማስፋፋት የሐዋርያት ሃላፊነት መሆኑን አፅንዖት በመስጠት ነው፡፡

የሐዋርያትን ሥራ ስናነብብ፣ በክርስቶስ ስለሚገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት በብሉይ ኪዳንና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ስለነበረው እምነት ካለው ዳራ በመነሣት እንደጻፈ ዘወትር ልብ ልንል ይገባናል፡፡ በተጨማሪም የሐዋርያት ሥራ በክርስቶስ የተጀመረው የመንግሥቱ ሥራ በሐዋርያትና በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን፣ በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍ የቀጠለ መሆኑን የሚዘግብ የሉቃስ ወንጌል ቀጣይ እንደሆነም ልናስታውስ ይገባናል፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ የሐዋርያት ሥራን ጸሐፊ ማንነት መርምረናል፤ ታሪካዊ መቼቱን ገልጸናል ደግሞም ነገረ-መለኮታዊ ዳራውን ዳስሰናል፡፡ እነዚህን ዝርዝሮች በልቡናችን ይዘን የሐዋርያት ሥራን ስናጠና ተቀዳሚ ትርጉሙን እንድንገነዘብና በሕይወታችንም በትክክል መተግበር እንድንችል ያግዘናል፡፡

ይህንን ተከታታይ ጥናት ስንቀጥል፣ የሐዋርያት ሥራ ዳራ በዚህ አስደናቂ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ለመመልከት የሚያስችሉ በርካታ መስኮቶችን እንደሚከፋፍትልን እንመለከታለን፡፡ ሉቃስ ስለመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን የጻፈው አብርሆተ-መለኮት ቴዎፍሎስና የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ታማኝ የሆነ አገልግሎት ለክርስቶስ ወደሚያቀርቡበት እርከን ይመራቸዋል፡፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዛሬም በዚህ ዘመን ለምትገኝበት ዓለም የመንግሥቱን ወንጌል ከማድረስ አንፃር ለምትተጋዋ ቤተክርስቲያን ወሳኝ መርሆችን የሚያቀርብ መሆኑን እንመለከታለን፡፡